# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 283 ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# «በፉክክር ሳይሆን በትብብር ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል»

- አቶ አገኘው ተሻገር
የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በፉክክር ሳይሆን በትብብር ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የፌዴራል ሥርዓት መገንባት እንደሚያስፈልግ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ። ክልሎች የሚያወጧቸው ህጎች ለክልላቸው ካለው ጠቀሜታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ሌሎች ክልሎች ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖም ታሳቢ ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የክልሎች የጋራ የምክክር መድረክ ትናንት በሀያት ሪጀንሲ ሆቴል ሲካሄድ ንግግር ያደረጉት አፈ ጉባኤው አቶ አገኘሁ ተሻገር፤ የውይይቱ ዋና ማጠንጠኛ ሀሳብ የመንግሥታት ግንኙነት መርሆች ናቸው። ህብረ ብሄራዊ የፌዴራል ሥርዓት እንዲጎለብት በማድረግ ህጋዊና ተቋማዊ ግንኙነት እንዲኖር ማስቻል አስፈላጊ ነው።

ካሁን በፊት እርስ በርስ ሲካሄዱ በቆዩ ግንኙነቶች


«በፉክክር ሳይሆን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







# በጎነት የዳበሳቸው ደሳሳ ጎጆዎች

**ታደሠ ብናልፈው**

የአብራካቸው ክፋይ የሆኑትን አራት ልጆቻቸውን ለማስተዳደር የጽዳት ስራ እየሰሩ የዕለት ጉርሳቸውን ለማሟላት ከህይወት ጋር ግብግብ የገጠሙ ሴት ናቸው፤ ወይዘሮ መሰረት ጉተማ።


በጎነት የዳበሳቸው ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


# ዘላቂ ሰላምን ለማጽናት ከማን ምን ይጠበቃል?

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ሰዎች በሕይወት ለመኖር ከምንም በላይ ሰላም ያስፈልጋቸዋል። የሕይወት ጎዶሎዎች የቱንም ያህል ሸንቁራቸው ቢበዛ ሰላም ካለ ሸንቁሩ መደፈኑ አይቀርም። ሰላም ካለ ረሃብ፣ ጥማቱ፣ መታረዝና መራቆቱ ቢኖር እንኳን ችግሩን ለማስተካከል እድል ይኖራል።

በተቃራኒው ደግሞ ሕይወት ያማረና የሰመረ ሁሉ ነገር የሞላላት ቢሆንና አገር ሰላም ብታጣ ትርጉም አይኖረውም። የሞላው ይጎድላል፤ የሰመረው ፍራቻን ይፈጥራል፤ የያዝነው ይበተናል። የነበረው ሁሉ


ዘላቂ ሰላምን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


# የክልሉች ትምህርት ተቋማት ደረጃ ዝቅተኛነት ለትምህርት ጥራት ተግዳሮት ሆኗል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በክልሎች ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያሉ የትምህርት ተቋማት የጥራት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆን የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ተግዳሮት ነው ሲሉ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ገለጹ።

የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱ ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት ውስጥ አንድ ነጥብ ሁለት በመቶ የሚሆኑት የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ሲሆኑ፤ ቀሪዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ አይደሉም። ጥራታቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ተግዳሮት ሆኗል።

በክልሉ አንድ ሺህ 241 የትምህርት ተቋማት እንዳሉ


የክልሉች ትምህርት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




አቶ አብዱ ሀሰን



አቶ ግርማ በደላ




# በኢትዮጵያ ከ23 በመቶ በላይ የሚሆኑ ሕፃናት ለአስከፊ ጉልበት ብዝበዛ ተዳርገዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከ23 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሕፃናት ለአስከፊ ጉልበት ብዝበዛ መዳረጋቸውን የአዲስ አበባ ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የኢንዱስትሪ ሰላም ዳይሬክተር አቶ ካሳ ስዩም እንዳስታወቁት፤ በኢትዮጵያ ብዙ ሕፃናት ጎጂና ከባድ ሥራ ውስጥ ተሰማርተው ይገኛሉ ። በአሁኑ ጊዜም 23 ነጥብ ሦስት በመቶ የሚሆኑ ሕፃናት ለአስከፊ ጉልበት ብዝበዛ ተዳርገዋል።

ሕፃናት ለአስከፊ ጉልበት ብዝበዛ በመዳረጋቸው ምክንያት ለአካላዊ፣ ለአእምሮዊና ለስነ- ልቦናዊ ጉዳት እየተዳረጉ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይ በህገወጥ ደላሎች ተታለው ከገጠር ወደ ከተማ መጥተው ለጉልበት ብዝበዛ የሚዳረጉ ሕፃናት ጉዳቱ ይበረታል ብለዋል።

እንደ አቶ ካሳ ገለጻ፡- በአገራችን የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ለማስቀረት በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ላይ የተደነገገ መመሪያ ቢኖርም በግንዛቤ ማነስ፤ በገንዘብ እጥረት እንዲሁም ለሕፃናት የልደት ሰርተፍኬት የመስጠት ሁኔታ በብዙ ቦታ የተለመደ ባለመሆኑ ችግሩን ውስብስብ አድርጎታል።

በሕፃናት ላይ እየደረሰ ያለውን አስከፊ የጉልበት ብዝበዛ መከላከልና ማስቀረት ለአንድ ለተወሰነ አካል የሚሰጥ ኃላፊነት ብቻ አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ጉዳቱን ለመቀነስ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ሁሉ ተሳትፎና ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ካሳ የሕፃናት ጉዳትን ለመቀነስ ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ተግባራዊ ማድረግ ይገባል ነው ያሉት።



በዓለም 168 ሚሊዮን ሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ ይፈጸምባቸዋል

በአሰሪና ሠራተኛ አዋጁ ከተቀመጠው ውጪ ሕፃናትን ቀጥረው የሚያሰሩና ለሰሩበት ተገቢውን ክፍያ ለማይከፍሉ ተቋማት የጉልበት ብዝበዛ እያደረጉ እንደሆነ በመገንዘብ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

ቢሮው በአሰሪና ሠራተኛ ዘርፍ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ 168 ሚሊዮን ሕፃናት በጉልበት ብዝበዛ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ በአፍሪካ 72 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ያህል የሚሆኑት ሕፃናት በጉልበት ብዝበዛ ውስጥ እንደሚገኙ በመድረኩ ተገልጿል።

በተጨማሪም በአፍሪካ በጉልበት ብዝበዛ ከሚገኙ ሕፃናት መካከል 31 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆኑት በአደገኛ ጉልበት ብዝበዛ ውስጥ ይገኛሉ። የአዲስ አበባ ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ እንዲኖር ለማስቻልና የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛን ለመቀነስ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ምክክር መደረጉ ይታወቃል።



አቶ ታደሰ ከበደ

## የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት የጀመሩ ተቋማት ግብይታቸውን በሚያዝያ ወር አጠናቀዋል

### - ከ10 ሺህ በላይ አቅራቢዎች በሥርዓቱ ተመዝግበዋል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን መጠቀም የጀመሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥዎችን በሚያዝያ ወር ማጠናቀቃቸውን የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ።

የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተም ፕሮጀክት ማናጀር አቶ ታደሰ ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ወደ ሲስተም የገቡት ተቋማት በተቻለ መጠን ግዢአቸውን ሰኔ ወር ከመድረሱ በፊት ባሉ ወራት ጨርሰዋል።

ሲስተሙ ተግባራዊ በመሆኑ አብዛኛው ግዥዎች በግልጽ እየተፈጸሙ ነው ያሉት አቶ ታደሰ፤ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ሐምሌ ወር ላይ ባቀዱት የግዥ እቅድ መሰረት ግዢአቸውን እንዲያከናውኑ እየተደረገ በመሆኑ ከዚህ ቀደም የነበሩ አላስፈላጊ ግዥዎችን መቀነስ ተችሏል ብለዋል።

ከዚህ በፊት የተለመደው ተቋማት የግዥ እቅዳቸው ውስጥ ሳይካተት በጀት በመትረፉ ብቻ አላስፈላጊ የሆኑ ግዥዎችን ይፈጽሙ እንደነበር ጠቁመው፤ በተያዘው ዓመት መሻሻል ታይቷል ብለዋል። ወደፊት ሁሉንም ተቋማት ወደ ሲስተሙ በማስገባት በበጀት ዓመት መጨረሻ የሚደረጉ አላስፈላጊ ግዥዎችን ለማስቀረት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

እንደ ፕሮጀክት ማናጀሩ ገለጻ፤ አብዛኛው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቀድመው ሚያዝያ ወር ላይ ግዥዎችን ፈጽመዋል። ይሁንና እንደ ግዥዎች አይነትና ባህሪ ክፍያዎች ተከፍለው ያላለቁ እንደሚኖሩ ጠቁመዋል።

አሁንም የሚፈጸሙ ግዥዎች እንዳሉ ገልጸው፤ ነገር ግን ግዥዎች የሚፈጸሙት በእቅዳቸው መሰረት ስለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር እየተካሄደ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።

ወደፊትም ሲስተሙ በሰኔ ወር ላይ ግዥ እንዳይፈጸም እንዲቆጣጠርና ተቆጣጣሪ አካላት እንዲያውቁት በማድረግ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚፈጸሙ አላስፈላጊ ግዥዎች ላይ ቁጥጥር እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

ከምንም በላይ የሰው አመለካከት መለወጥ አለበት ያሉት አቶ ታደሰ፤ የሚበላሸው የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት በመሆኑ የማይፈለግ ግዥ መፈጸም የለበትም፤ የመንግስት ግዥ የውስጥ ሀብት አልበቃ ሲል የሚደረግ የመጨረሻ አማራጭ እንጂ በጀት ስለተረፈ ብቻ የሚደረግ ግዥ መሆን የለበትም ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ ከ10 ሺህ በላይ አቅራቢዎች በመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ግዢ ሲስተም መመዝገባቸውን የገለጹት ማናጀሩ፤ ከዓመት በፊት 50 አቅራቢዎች ብቻ ተመዝግበው እንደነበር አንስተዋል። በ2016 ቁጥሩን ለመጨመር እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በተያዘው ዓመት ሁለት ሺህ 500 ጨረታዎች በሲስተሙ መውጣታውን እና ይህም ለገዥዎች ሰፊ እድል በመፍጠር የግዥ ሥርዓትን ማቀላጠፉን ያብራሩት አቶ ታደሰ፤ የንግዱ ማህበረሰብ በስፋት ሲስተሙን እንዲጠቀምና መሥሪያ ቤቶች ቀድመው በእቅዳቸው መሰረት በመጀመሪያው በጀት ዓመት ግዢአቸውን እንዲፈጽሙ ጥሪ አቅርበዋል።



## የወላይታ ዞን ዳግም ሕዝበ ውሳኔ በትናንትናው እለት ተካሄደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የወላይታ ዞን የድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የድምፅ መስጠት ሂደት ትናንት ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔውን አስመልክቶ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የወላይታ ዞን የድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የድምፅ መስጠት ሂደት ትናንት ማለዳ 12፡00 ተጀምሯል።

ቦርዱ የድጋሚ ህዝበ ውሳኔውን የሚያከናውኑ የምርጫ አስፈፃሚዎችን በተለያየ መንገድ የመለመለ ሲሆን፤ ከአዲስ አበባ 5 ሺህ 215 የምርጫ አስፈፃሚዎች እና ከወላይታ 3 ሺህ 845 የምርጫ አስፈፃሚዎች መሳተፋቸውንም አስታውቋል።

በትናንትናው እለት ሁሉም አስፈፃሚዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው መራጮችን አስተናግደዋል ያለው ቦርዱ፤ አንዳንድ ሰልፎች የበዙባቸው ጣቢያዎች ላይ ቦርዱ አሰልጥኖ በተጠባባቂነት የያዛቸው አስፈፃሚዎች መሰማራታቸውን አስታውቋል፤ በ1 ሺህ 812 የምርጫ ጣቢያዎች የተሟላ የምርጫ ቁሳቁሶች መድረሳቸውንም አረጋግጧል።

ከጠዋት 12፡00 ሰዓት እስከ 6፡00 ሰዓት በተገኘው መረጃ 370 ሺህ 552 መራጭ ድምፅ ሰጥቷል ያለው ቦርዱ፤ በተያያዘም የድምፅ መስጠት ሂደት ቦርዱ ለሶስት የሀገር ውስጥ ተቋማት የታዛቢነት እውቅና ሰጥቶ በዞኑ የተለያዩ ጣቢያዎች ላይ 214 ታዛቢዎች ማሰማራቱን ገልጿል።

የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ በርካታ መራጮች 6 ወር ያልሞላው መታወቂያ ይዘው መገኘታቸውን ቦርዱ ጠቅሶ፤ ነገር ግን የቦርዱ መመሪያ አንድ ዜጋ ድምፅ መስጠት የሚችለው በመኖሪያ ስፍራው ቢያንስ ለስድስት ወር እና ከዚያ በላይ መኖሩ ሲረጋገጥ መሆኑን ጠቅሷል።

ስለዚህ እነዚህ መራጮች ከያዙት የነዋሪነት መታወቂያ በተጨማሪ ነዋሪነታቸውን የሚያረጋግጡበት የሦስት ሰዎች ምስክርነት ወይም ሌሎች የሠነድ ማስረጃዎችን በማቅረብ ድምፅ እንዲሰጡ ማድረጉን ቦርዱ አስታውቋል።

በወላይታ ዞን የተደረገው ህዝበ ውሳኔ “መጠነ ሰፊ” ጥሰቶች ተፈጽሞባቸዋል በመባሉ የመራጮች ምዝገባ ውድቅ ተደርጎ በድጋሚ እንዲካሄድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መወሰኑ ይታወሳል። በዚህም መሰረት በትናንትናው እለት በዞኑ ዳግም ሕዝበ ውሳኔ ተካሂዷል።



ዶክተር ሊያ ታደሰ

# ከ56 ሚሊዮን

## በላይ ዜጎች የጤና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ ሆነዋል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ ፡- በኢትዮጵያ ከ56 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የማህበረሰብ የጤና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ መሆናቸውን የጤና ሚኒስቴር ገለጸ።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ ሰሞኑን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና መድህን ተደራሽነትና የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸምን በተመለከተ በተደረገው ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ከ56 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የማህበረሰብ ጤና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል። ከእነዚህም ውስጥ ከስምንት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ዜጎች የመክፈል አቅም የሌላቸው በመሆኑ ዓመታዊ መዋጮአቸው በክልል መንግሥታት የተሸፈነላቸው ናቸው።

ሁሉን አቀፍ የጤና መድህን አገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በተለይም ዜጎች ለህክምና የሚያወጡትን ከፍተኛ የወጪ ጫና በማስቀረት ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ የኤጀንሲው ዋና ዓላማ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የማህበረሰብ ጤና መድህን በአገሪቱ ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ 987 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

ለማህበረሰቡ ለህክምና ያልተገባ ክፍያ በማስቀረት ወደ ድህነት የሚገባውን የህብረተሰብ ክፍል መታደግ የሚያስችለው ይህ የመድህን አገልግሎት ለህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን የተለያየ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን አውስተው፤ በ775 ወረዳዎች ማህበረሰብ አቀፍ ጠቅላላ ጉባኤ መድረክ መካሄዱንም ተናግረዋል።

በ2015 ዓ.ም የአባልነት ምጣኔ 80 በመቶ እና የእድሳት ምጣኔ 90 በመቶ መድረሱ፣ ህብረሰተቡ ስለጤና መድህን ያለው ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ አንዱ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል።

ዶክተር ሊያ እንደገለጹት፤ የማህበረሰብ ጤና መድህን አገልግሎት በ2013 ዓ.ም በተሰራው የተጽእኖ ጥናት መሰረት የማህበረሰብ የጤና መድህን የተተገበረባቸው ወረዳዎች ላይ የህብረተሰቡ የህክምና ወጪ ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር ከ28 እስከ 43 በመቶ ያነሰ መሆኑን ያሳያል። መርሃ ግብሩ ከመጀመሩ በፊት የነበረው ተጠቃሚነት የአገልግሎት አጠቃቀም ምጣኔ ከ0 ነጥብ 36 ወደ ሁለት በመቶ መድረስ መቻሉንም ተናግረዋል።

በሀገሪቱ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ሽፋን ከ90 በመቶ በላይ ቢሆንም የህብተሰቡ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት ከፍተኛ አይደለም። ይህንን ለማሻሻልም የጤና መድህን ሥርዓት መዘርጋት ፍትሐዊ አጠቃቀምና ተደራሽነት እንዲኖር የራሱ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

የአባላት ምዝገባ እና እድሳት በየዓመቱ ከመስከረም እስከ የካቲት የሚደረግ መሆኑን ገልጸው፤ ማህበረሰቡም የመድህን አባል በመሆን ለህክምና ከሚያወጣው ከፍተኛ ወጪ እና የመድኃኒት አቅርቦት ችግርን በመቅረፍ ጥራት ያለው አገልግሎት ለማግኘት እንደሚረዳው በመረዳት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ዶክተር ሊያ ጥሪ አቅርበዋል።

# በትግራይ የሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎች

## ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችላቸው ቁመና ላይ ደርሰዋል

**እፀገነት አክሊሉ**

አዲስ አበባ ፡- በትግራይ ክልል የሚገኙት አራቱ ዩኒቨርሲቲዎች በአሁኑ ወቅት ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችላቸው ቁመና ላይ መድረሳቸውን የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአስተዳደርና መሰረተ ልማት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰለሞን አብርሃ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳሉት፤ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወደ ሥራ መግባታቸው አንዱ ለሰላም ስምምነቱ ተፈጻሚነት ማሳያ በመሆኑ እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ወዲያውኑ ኮሚቴ በማዋቀርና ወደ መቀሌ በመሄድ ተቋማቱ ያሉበትን ሁኔታ የማየት ሥራ ተከናውኗል፤ በአሁኑ ወቅትም ዩኒቨርሲቲዎቹ ወደ ስራ የሚገቡበት ቁመና ላይ ይገኛሉ።



ፎቶ - አጋፔ ገዮን

ዶክተር ሰለሞን አብርሃ

እንደ ዶክተር ሰለሞን ገለጻ ኮሚቴው የአራቱን ዩኒቨርሲቲ አመራሮች በመጥራት ያሉበትን ሁኔታ የደረሰባቸውን ጉዳትና ሊደረግ በሚገባው ድጋፍ ዙሪያ ውይይት አድርጓል፤ እነሱም አለ ስለሚሉት ነገር ሪፖርት አቅርበዋል። በዚህም መሰረት ተቋማቱን ወደ ስራ ለማስገባት አስፈላጊ ነገሮች ተከናውነዋል።

እንደ ትምህርት ሚኒስቴርም አክሱም ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል የሚል መረጃ ስለነበረ በቦታው ላይ ቅኝት የሚያደርግ ቡድን በመላክ ሁለት ሳምንት ቆይታ በማድረግ አጠቃላይ ሁኔታውን የገመገሙ ሲሆን፣ የትምህርት ክፍሎቹን አዲሱ አመራር እንዲረከብ የማድረግና የጽዳት ሥራዎች ተሰርተው ወደ ሥራ እንዲመለስ የማድረግ ተግባር መከናወኑን አብራርተዋል።

በአሁኑ ወቅትም ዩኒቨርሲቲዎቹ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችላቸው ቁመና ላይ እየደረሱ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ሰለሞን፤ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ ሲገቡ ምግባቸውም ሆነ ማደሪያቸው እንዲሁም የጤና ሁኔታቸው ሁሉ ክትትል የሚደረገው በመንግሥትና በተቋማቱ በመሆኑ በእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች ሲገቡ እነዚህ ነገሮች ተሟልተው ሊጠብቋቸው ስለሚገባ ባለፉት ወራቶች ከትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም ከአካባቢው አመራሮች ጋር በመሆን እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ላይ በዩኒቨርሲቲው ይማሩ የነበሩ ከ20 ሺ በላይ ተማሪዎች ከትግራይ እንዲወጡ በማድረግ በጊዜያዊነት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ፤ መመረቅ የነበረባቸውም እንዲመረቁ የሚቀራቸውም እንዲማሩ ተደርጓል ያሉት ዶክተር ሰለሞን፤ ነገር ግን ከ20 ሺ በላይ ከትግራይ ያልወጡ የአካባቢው ተማሪዎች ነበሩ ብለዋል። አሁን እነዚህን ተማሪዎች ካቆሙበት የማስቀጠል በቀጣይም የአዲስ ተማሪዎችን ቅበላ የሚጀምሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ስራው እየተሰራ ስለመሆኑ ጠቁመዋል።

አሁን ላይ ራያ ዩኒቨርሲቲ እዛ አካባቢ ያሉትንና ሌላ ቦታ ያልተመደቡትን ነባር ተማሪዎችን ጠርቶ ምዝገባ እያደረገ ነው። መቀሌና አዲግራትም ከአንድ ወር በኋላ ወደ ሥራ የሚገቡ ሲሆን፤ አክሱም ዩኒቨርሲቲ የዛሬ ሁለት ወር ወደመማር ማስተማር ስራው ይገባል። ሁሉም ግን ለነባር ተማሪዎቻቸው ጥሪ ከማስተላለፍም በላይ ባሉበት ሆነው ምዝገባቸውን እንዲጨርሱም አድርገዋል ብለዋል። በዚህም ያላቸውን የተማሪ ቁጥርና ሊያደርጉ የሚገባቸውን ዝግጅት አውቀዋል፤ ጊዜው ሲደርስ ጠርተው ያስገባሉ ብለዋል።

በወቅቱ ተፈናቅለው የመጡ መምህራን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ስራቸውን እንዲጀምሩ ሆኗል። ነገር ግን አሁን ላይ ሁኔታዎች እየተስተካከሉ በመሆኑ ወደቀድሞ ዩኒቨርሲቲዎቻቸው ተመልሰው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ጥሪ እናደርጋለን ሲሉም አብራርተዋል።

# ብሪታንያ ኢትዮጵያን ጨምሮ 65 አዳጊ አገራትን

## ተጠቃሚ የሚያደርግ የንግድ ስልት ይፋ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ብሪታንያ ኢትዮጵያን ጨምሮ 65 አዳጊ አገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ የንግድ ስልት ይፋ አድርጋለች። በኢትዮጵያ የንግድ ስልቱን የማስጀመሪያ መርሐ ግብር በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በመርሐ ግብሩ ንግግር ያደረጉት የብሪታንያ ዓለም አቀፍ ንግድ ሚኒስትር ኒገል ሀድልስቶን፤ ይህ አዲስ የንግድ ስልት ለአዳጊ አገራት የንግድ ቀረጥን የሚቀንስ ነው ብለዋል።

በዚህ የንግድ ማዕቀፍ ተጠቃሚ የሚሆኑት ኢትዮጵያን ጨምሮ 65 አዳጊ አገራት በጥቅል ወደ ብሪታንያ በየዓመቱ ከሚልኩት 20 ቢሊዮን ፓውንድ የሚያወጣ ምርቶቻቸው ተጠቃሚ ይሆናሉም ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሥራ አስፈፃሚ አክሊሉ ታደሰ በበኩላቸው፤ የንግድ ሥርዓቱ በተለይ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመረቱ ምርቶች በቀላሉ ወደ ብሪታንያ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰዋል።

የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሜ፤ የንግድ ስልቱ የሁለትዮሽ የንግድ ትስስር በመፍጠር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማበረታታት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት መፋጠን ጉልህ ሚና እንደሚጫወት አስረድተዋል።

የንግድ ስልቱ መጀመር ኢትዮጵያ ያሏትን ፀጋዎች በመጠቀም የምታመርታቸውን ምርቶች ለዓለም ከማስተዋወቁም በላይ የተጀመረውን የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል ያሉት ደግሞ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ ሀሰን መሐመድ ናቸው።



የልዑካን ቡድኑ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉብኝት አድርጓል

በዚህ የንግድ ስልት ተጠቃሚ ከሚሆኑ 65 አዳጊ አገራት መካከል 37ቱ የአፍሪካ አገራት ሲሆኑ፤ 3 ነጥብ 3 ቢሊዮን ያክል ሰዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በተያያዘም በብሪታንያ የንግድ ሚኒስትር ኒጌል ሀድልስቶን የተመራ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት አካሂዷል።

ልዑኩ በቀጣይ የብሪታንያ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ እንደሚመክር የኮርፖሬሽኑ መረጃ ያመላክታል።

ከውይይቱ በኋላም የእንግሊዝ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት በሚሰማሩበት ሁኔታ እና ሌሎች ጉዳዮች ከኮርፖሬሽኑ ጋር በቀጣይ መሥራት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ ከስምምነት ላይ ይደርሳሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ኤፍቢሲ ዘግቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻሉ አገራዊ ንቅናቄ የሁሉንም ተሳትፎ ይጠይቃል!

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በኢትዮጵያ ካሉ ከ49 ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ86 በመቶ በላይ የአንደኛ እና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ እንዲሁም ከ71 በመቶ በላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ-ልማቶች በተሟላ ደረጃ የላቸውም።

ለምሳሌ፣ በአገሪቱ ካሉት ትምህርት ቤቶች 33 ነጥብ ሁለት በመቶ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና 55 ነጥብ67 በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ የንጹህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት አላቸው። 37 በመቶ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም 43 በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ የመፀዳጃ አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው።

29 ነጥብ አራት በመቶ አንደኛ እና መካከለኛ 74ነጥብ አምስት በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ተጠቃሚ ሲሆኑ፤ የተቀሩት በቴክኖሎጂ የተደገፈ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የትምህርት ክህሎትን እንዲያዳብሩ ለማድረግ የሚሰራውን ሥራ ፈታኝ አድርጎባቸዋል።

ይሄ ደግሞ ተማሪዎች በተጓደለ የትምህርት ከባቢ ውስጥ እንዲማሩ ያስገደዳቸው ከመሆኑም በላይ፤ በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው የሚጠበቅባቸውን እውቀት፣ ክህሎትና የባህሪ ለውጥ ማምጣት እንዳይችሉ አድርጓል።

ከዚህ አኳያ የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች የትምህርት ጥራት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ያሳዩ ሲሆን፤ በ2014 ዓ.ም የተደረገው አገራዊ ፈተና ውጤትም ለዚሁ ማረጋገጫ የሰጠ ሆኗል።

ይሄ የጥራት ችግር ለመንሰራፋቱ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ በርካታ መንስኤዎች ቢኖሩም፤ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ያለመሆንን የሚመለከተው እና የአገራችንን ትምህርት ቤቶች ደረጃ አልባ ያደረገው የትምህርት ቤቶች ግብዓትና መሰረተ ልማት አልቦነት ነው።

ይሄ ሃቅ ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፤ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ ነገን እውን ለማድረግ አቅደው እየተጉ ያሉትን ሁለንተናዊ የብልጽግና ጉዞን የሚፈትን ነው። ምክንያቱም ትምህርት ለሰው ልጆች የእውቀትም፣ የክህሎትም፣ የሥነ ምግባርም፣ በጥቅሉ ከፍ ያለ የሰው ልጅን ምሉዕነት የመፍጠሪያ አውድ እንደመሆኑ፤ ይሄንን ምሉዕነት መፍጠር የማይችሉ ትምህርት ቤቶችን ይዞ የብልጽግናውን ግብ ለማሳካት የሚደረገውን ጉዞ በብቃት የሚያሳልጥ ትውልድ መፍጠር አይቻልም።

በመሆኑም ይሄንን ጉዞ ለማሳለጥ፣ ለዚህ የሚሆን ትውልድን በትምህርት ቤቶች ለመፍጠር ካስፈለገ፤ የእነዚህን ትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሻሻል፤ በተገቢው ግብዓትና መሰረተ ልማት ማደራጀት እጅጉን አስፈላጊ ነው።

ይሄንንም መንግሥት በተለይም ዘርፉን የሚመራው ትምህርት ሚኒስቴር ተገንዝቦ እንቅስቃሴ ጀምሯል። ይሁን እንጂ ይሄንን ችግር መፍታት እና እነዚህን ትምህርት ቤቶች የሚፈለገው ደረጃ ላይ የማድረስ ሥራው በመንግሥት አቅም ብቻ በሚፈለገው ጊዜና ሁኔታ እውን ማድረግ አይቻልም።

ይሄን በተመለከተ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ችግሩን በመንግሥት አቅም ብቻ ለመፍታት ቢታሰብ ከሦስት አስርት አመታት ያላነሰ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ስለዚህ “ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፣ ለሃምሳ ሰው ጌጡ” እንዲሉ፤ ይህን ሰፊ ችግር መፍታት የሚቻለው ሥርዓት ዘርግቶ በዘላቂነት ሰፊውን ሕዝብ እና ልዩ ልዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላትን ቀጥተኛ ተሣትፎን ያረጋገጠ ንቅናቄ በማድረግ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ አንፃር ትምህርት ሚኒስቴር አገር አቀፍ ንቅናቄ የማድረግ እቅድ የያዘ ሲሆን፤ በዚህ ንቅናቄ መሰረት በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ የአካባቢው ማኅበረሰብ፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ በትምህርት ዘርፉ ላይ የሚሰሩ የውስጥም የውጪም ተቋማትና ድርጅቶች፣ በትውልድ ቦታቸው፣ በተማሩበት ቦታ፣ በሚሰሩባቸውና በሚኖሩባቸው አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት በሚችሉት መንገድና መጠን አስተዋጽኦ በማድረግ አሻራቸውን የሚያሳርፉበት ሁኔታ አመቻችቷል።

የዚህ ንቅናቄ ተጠባቂ ውጤትም፣ በማኅበረሰብና በልዩ ልዩ አካላት አስተዋጽኦና ጥረት እያደጉ የመጡ መሠረተ ልማታቸውን (ንጹሕ ውሃ፣ መፀዳጃ ክፍሎች፣ በቂ መማሪያ ክፍሎች፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፤ የስፖርት ሜዳ፣ መጻሕፍት፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ ቤተ-ሙከራ፣ ወዘተ.) ያሻሻሉ ትምህርት ቤቶች በብዛት እንዲኖሩ ማድረግ ነው።

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ማሻሻል ንቅናቄ ዋና ዓላማ አድርጎ ከተነሳባቸው ጉዳዮች መካከል፤ ትምህርት ቤቶችን ከሦስቱ አበይት ጉዳዮች አንፃር በመገምገምና ችግሮችን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ትምህርት ቤቶች ያለባቸውን ክፍተቶች በመፍታት የተማሪዎችን ውጤትና ሥነምግባር ማሻሻል ላይ ያተኮረ ነው። ከእነዚህም መካከል፣ በስታንዳርድ መሰረት የተሟላ ቤተ መጻሕፍት፣ የቤተ-ሙከራ አገልግሎት እንዲሁም የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው።

በመሆኑም ሁሉም ዜጋ የንቅናቄው ንቁ ተሳታፊ በመሆን የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት ለማሻሻል፤ እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት በባለቤትነት በመደገፍ የነገ አገር ተረካቢ ትውልዶች በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በሥነምግባርና በሞራል ተገንብተው የሚወጡባቸውን ትምህርት ቤቶች የመፍጠር ኃላፊነቱን በብቃት ሊወጣ ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ትምህርት ቤቶችን በማሻሻል በልጆቻችን ነገ ላይ አሻራ እናኑር

ማሙሻ ከአቡርሻ

አበው «የበላ እና የተማረ ወድቆ አይወድቅም» ይሉት ብሂል፤ አንድም የበላ ጉልበቱ በቀላሉ ለዳገትም፣ ለድካምም እጅ አይሰጥም፤ አንድም የተማረ ለችግርና ፈተና መሻገሪያ መላ ከአዕምሮው ጓዳ እንደማይጠፋ ለማመልከት ነው። አንጋፋው ሙዚቀኛ አለማየሁ እሸቴም፣ በዜማው «ተማር ልጄ፣ ዘመድ አዝማድ የለኝ ሀብት የለኝም በእጄ፤» ሲል ለልጁ ብርቱ ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ በግጥም ስንኞቹ ውስጥ ማኖሩ ይሄንኑ የትምህርትን ችግር አሻጋሪነት፤ ሀብትና ፀጋ አጎናጻፊነት የሚያስገነዝብ ነው።

እነዚህ እና ሌሎችም በብሂልም፣ በስንኝም የምናገኛቸው የመማርን ከፍ ያለ ዋጋ የሚያስረዱ አገራዊ ታሪኮች ታዲያ፤ ትምህርት በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ምን ያህል ከፍ ያለ ቦታም፣ አቅምም እንዳለው የሚያረጋግጡ ናቸው። እርግጥ ነው ዓለምም በተማሩና በተመራመሩ ሕዝቦቿ ነው ዛሬ ላይ ከረቀቁት እስከ ገዘፉት የፈጠራ ቴክኖሎጂዎች ታግዛ የተወሳሰቡ ችግሮቿን መፍታት የምትችልበትን አቅም የተጎናጸፈችው።

በአገራችን ኢትዮጵያም ይሄው ዘመናትን ያስቆጠረው የቀለም አውድ (ቀድሞ በቤተ እምነቶች፣ ኋላም በዘመናዊው አስኳላ) ዜጎች ፊደል ከመቁጠር እስከ መመራመርና ፈጠራ የሚያዘልቃቸውን አቅም እንዲሰንቁ ሲያደርግ ቆይቷል። እያደረገም ይገኛል። ይሁን እንጂ ይሄ የተመራማሪነት እና የፈጠራ አቅምን የሚያጎናጽፈው ትምህርት፤ የሚፈለገውን አቅምና ክህሎት ለተማሪዎች ማጎናጸፍ አልቻለም። ከዚህ የተነሳም በትውልዶች ሆነ ከዚህ በሚመነጭው የአገር ግንባታ ላይ ትልቅ ተግዳሮት ሆኗል።

በዚህ ረገድ በአገራችን ኢትዮጵያ አፍ ሞልቶ «ትምህርት ድሮ ቀረ» ሊያስብል የሚያስችል በሁሉም መልክ የተደራጁ ትምህርት ቤቶች አሉ ባይባልም፤ አሁንም «ትምህርትስ ድሮ ቀረ» የሚሉ ቀደምቶች አልታጡም። ለዚህ እንደ ምክንያት የሚያቀርቡትን የቀደመው ትምህርት ከግብዓቱም ይሁን ከትምህርት ሥርዓቱ ይሄ ነው ብለው ባይለዩትም፤ ተማሪዎቹ ግን በእውቀትም፣ በአስተሳሰብ ብስለትም ከአሁኑ ቀለሜ ሻል ያሉ ስለመሆናቸው ይሞግታሉ።

ይሄ የቀደምቶች ብሂል እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዛሬ ላይ ሊካድ የማይገባው ሃቅ ግን ትምህርት ቤቶች የቁጥራቸውን ያህል በሚፈለገው መጠን የተደራጁ እና ለመማር ማስተማር ብቁ መሆን አለመቻላቸው ነው። ይሄንኑ እውነት መንግሥት በተለይም ዘርፉን የሚመራው ትምህርት ሚኒስቴር ደጋግሞ እወቁልኝ ያለ ሲሆን፤ ዛሬ ላይ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ዘመኑን በሚመጥኑ እና የተማሪዎችን ሁለንተናዊ አቅም ከሚገነቡ ትምህርት ቤቶች ይልቅ፤ በጭቃ ቤት፣ በዳስ እና በዛፍ ጥላ ስር ተማሪዎችን አስጠልለው «እውቀት ቅሰሙ» የሚሉ ስለመሆናቸው በመረጃም፣ በማስረጃም አስደግፎ ገልጿል።

> **ዛሬ ላይ ሊካድ የማይገባው ሃቅ ግን ትምህርት ቤቶች የቁጥራቸውን ያህል በሚፈለገው መጠን የተደራጁ እና ለመማር ማስተማር ብቁ መሆን አለመቻላቸው ነው። ይሄንኑ እውነት መንግሥት በተለይም ዘርፉን የሚመራው ትምህርት ሚኒስቴር ደጋግሞ እወቁልኝ ያለ ሲሆን፤ ዛሬ ላይ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ዘመኑን በሚመጥኑ እና የተማሪዎችን ሁለንተናዊ አቅም ከሚገነቡ ትምህርት ቤቶች ይልቅ፣ በጭቃ ቤት፣ በዳስ እና በዛፍ ጥላ ስር ተማሪዎችን አስጠልለው «እውቀት ቅሰሙ» የሚሉ ስለመሆናቸው በመረጃም፣ በማስረጃም አስደግፎ ገልጿል**

በእንዲህ ዓይነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚከናወን የመማር ማስተማር ሂደት ደግሞ ተማሪዎችን ትምህርት ቤት ውለን መጣን ከሚል እሳቤ የዘለለ፤ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ይሄንን እውቀት ቀሰምኩ፣ ይሄንን አዲስ ክህሎት አዳበርኩ ብለው የሚጠቅሱት ተደማሪ አቅም ማግኘት አይችሉም። ይሄንኑ ሃቅ የሚያረጋግጥልን ደግሞ፣ የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች የትምህርት ጥራት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ማሳየታቸው ነው።

ለምሳሌ፣ በርካታ ትምህርት ቤቶቹ ከደረጃ በታች ብቻ ሳይሆን የዳስ እንደሆኑ የሚነገርለት የአማራ ክልል፤ ከሁለትና ሦስት ዓመታት በፊት የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በክልሉ ከሚገኙ ዘጠኝ ሺ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሰባት ሺህ ያህሉ ከደረጃ በታች ናቸው። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ከደረጃ በታች ከመሆናቸው ባሻገር ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የዳስ ትምህርት ቤቶች ናቸው። መደበኛ የሚባሉት ትምህርት ቤቶችም ቢሆኑም የወንበር፣ በር፣ መስኮትና ጥቁር ሰሌዳ ሳይቀር በተሟላ መንገድ የሌላቸውና ለመማር ማስተማሩ ሥራ ምቹ ያልሆኑ ናቸው።

በመሆኑም እነዚህን ትምህርት ቤቶች ከዳስ ትምህርት ቤትነት ከፍ ለማድረግ እንዲሁም አስፈላጊው ግብዓት እንዲሟላላቸው ለማድረግ የተወሰነ እንቅስቃሴ ተደርጎ ነበር። በዚህ እንቅስቃሴም በክልሉ አንድ ሺህ የሚደርሱ የዳስ ትምህርት ቤቶችን በጊዜያዊነት ወደ ቆርቆሮ መቀየር የተቻለ ሲሆን፤ በዚህ ሂደት የመንግሥት አቅም ውስን እንደመሆኑ ባለሀብቱ የራሱ አበርክቶ ነበረው። በዚህ ረገድ ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ አንድ የዳስ ትምህርት ቤትን ዘመናዊና ግብዓት ወደተሟላለት ትምህርት ቤት ቀይሮ ለተማሪዎችም ለወላጆችም እፎይታን መፍጠር፤ በትውልድ ግንባታ ሂደትም ተደማሪ አሻራውን ማኖር የቻለበት ሃቅ ተጠቃሽ ነው።

በአማራ ክልል በዚህ መልኩ የተነሳው መረጃና ተግባር ከሰሜኑ ጦርነት በፊት የነበረ ሲሆን፤ ጦርነቱ በትምህርት ተቋማትና ሌሎችም ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ያሳደረ እንደመሆኑ ከዚያ በኋላ የትምህርት ቤቶቹ ሁኔታ ወዴት ሊያሽቆለቁል እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ ከዳስነት ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤትነት የለወጠው ትምህርት ቤት ላይ የደረሰው ጉዳት ደግሞ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው።

ለሁለት ዓመታት የዘለቀው የሰሜኑ ጦርነት አማራ ክልልን ብቻ ሳይሆን ትግራይ እና አፋር ክልሎች ላይም ከፍ ያለ ጉዳትን ያስከተለ ነው። ከዚህ ባለፈም በኦሮሚያ፣ ደቡብ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎችን ጨምሮ በበርካታ የኢትዮጵያ ክፍሎች በነበሩ ግጭቶች ትምህርት ቤቶች የጥፋቱ ሰለባ ሆነዋል። በዚህም በሺዎች የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች ለከፋ ጉዳት የተዳረጉ ሲሆን፤ እነዚህን መልሶ ለማደራጀትና ወደሥራ ለማስገባት ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወነ ስለመሆኑም መገለጹ ይታወቃል።

ወደ 11ኛ ገጽ ዞሯል

# «በፉክክር ሳይሆን በትብብር ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የታዩትን ጥንካሬዎች በማስቀጠል ያጋጠሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ክፍተቶችን በመሙላት የክልል መንግሥታት የነበራቸውን ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር የሚያስችል ምክክር ማካሄድ አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ አገኘሁ፤ ይህም የፌዴሬሽን ምክር ቤትና ክልሎች በአዋጁ ተዘርዝረው በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ይበልጥ ሚናቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ያለመ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አፈ ጉባኤው ገለጻ፤ በፌዴራላዊ ሥርዓተ መንግስት ውስጥ በመንግሥታት መካከል የሚካሄዱ የእርስ በርስ ምክክሮችና የሚደረጉ የትብብር ስምምነቶች በክልል መንግሥታቱ መካከል ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለማስቀረት፣ ግጭቶች ተከስተው ሲገኙ ተነጋግሮ ለመፍታት፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች እንዲናበቡና በሁሉም ክልሎች ተቀራራቢ አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል። የጋራ አስተሳሰቦችን በመያዝና በማጠናከር በየጊዜው እየጎለበተ የሚሄድበትን አሠራር ለመዘርጋት ወሳኝ መሣሪያ ተደርገው እንደሚወሰዱ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

በውድድርና በፉክክር ሳይሆን በትብብር ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ስርዓት እንዲገነባ በክልሎች መካከል ጤናማ ግንኙነት ሊኖር ይገባል ያሉት አቶ አገኘሁ፤ ጠንካራ የፌዴራል ሥርዓት ለማስፈን በውይይትና በመግባባት ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ሥርዓት ሊኖር ይገባል፤ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ሥርዓት መኖር አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ክልሎች ህጎችን የማውጣት ሉአላዊ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ያሉት አፈ ጉባኤው፤ የሚያወጧቸው ህጎች ለክልላቸው ካለው ጠቀሜታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ሌሎች ክልሎች ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ታሳቢ ሊያደርጉ እንደሚገባቸውም ተናግረዋል። በፌዴራል ተቋማት ላይ ምን አስተዋጽዖና ተፅዕኖ አለው የሚለው ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት። በመድረኩም ክልሎች ያላቸውን ሃሳብ በማንሳት ውይይት የሚያደርጉበትና የጋራ ሃሳብ የሚይዙበት መሆኑን ጠቅሰዋል።

አፈ ጉባኤው ህብረ ብሄራዊ የፌዴራል ሥርዓት ስር እንዲሰድ በፌዴራል መንግሥት እና በክልሎች፣ እንዲሁም በራሳቸው በክልሎች መካከል ሲደረግ በቆየው ኢ- መደበኛ ግንኙነት የታዩትን ጥንካሬዎች ማስቀጠል ያስፈልጋል። ያጋጠሙ ወይም ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ክፍተቶችን በመሙላት ፌዴራላዊ ሥርዓቱንም ሆነ የሀገሪቱን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለማጠናከር ሕጋዊና ተቋማዊ የሚያደርግ የመንግሥታት የግንኙነት ሥርዓትን ለመወሰን አዋጅ ቁጥር 1231/2013 ፀድቆ ስራ ላይ ውሏል ብለዋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመንግሥታት ግንኙነት፣ የዴሞክራሲያዊ አንድነትና የሕገመንግሥት አስተምህሮ ቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ወይዘሮ ባንቺይርጋ መለሰ፤ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ የመንግስት አደረጃጀት ሥርዓትን የምትከተል እንደመሆኗ መጠን ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲን ለማረጋገጥ፣ ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ለማስቀጠልና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመገንባት መደበኛ የመንግሥታት ግንኙነቶች መኖር አስፈላጊ ነው ብለዋል።

‹‹መንግሥታት ግንኙነት ተሞክሮ በኢትዮጵያና ቀጣይ አቅጣጫ›› በሚል የመወያያ ጽሁፍ ያቀረቡት በፌዴሬሽን ምክር ቤት የስትራቴጂካዊ ጉዳዮች አስተባባሪና ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ በላይ ወዲሻ፤ የፌዴራል ሥርዓት ባህሪ የፌዴራልና የክልል መንግስታትን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚፈልግ ነው። ይህም ስልጣን በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መካከል የሚደረግ የስልጣን ክፍፍል በመኖሩ ነው። ስለሆነም የፌዴራልና የክልል መንግሥታት በመመካከርና በመነጋገር የሚሰሩባቸው አግባቦች መኖር አለባቸው፤ መድረኩም የፌዴራል ሥርዓቱ ህይወት እንዲኖረው ከፍተኛ ሚና አለው ብለዋል።

# የክልሎች ትምህርት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የጠቆሙት ኃላፊው፤ ከነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ ቤተ-መጽሐፍት፣ የመፀዳጃ ቤት፣ ንፁህ የመጠጥ ውሀ፣ ቤተ-ሙከራ፣ የሙቀት ማቀዝቀዣ፣ መብራት፣ የሴቶች የግል ንፅህና መጠበቂያ እና የመሳሰሉ መሰረታዊ ግብአቶችን ያሟሉ ባለመሆናቸው የትምህርት ጥራትን ለማምጣት አሉታዊ ጉዳት እያደረሱ ነው ብለዋል።

አቶ አብዱ አከለውም፤ ሴት ተማሪዎች የግል ንፅህና መጠበቂያና መቀየሪያ ክፍል በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች ባለማግኘታቸው ከትምህርት ገበታቸው ይቀራሉ ሲሉ አብራርተዋል።

ክልሉ በአብዛኛው ሞቃታማ ስፍራዎችን የያዘ ቢሆንም ቁጥራቸው ከ70 እስከ 80 የሚሆኑ ተማሪዎች በአንድ ክፍል እየተማሩ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ ያለውን ችግር በመቅረፍ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የትምህርት ተቋማትን ደረጃ ማሻሻልና ማጎልበት ይገባል ሲሉ አመላክተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ግርማ ባይሳ በበኩላቸው፤ የትምህርት ጥራትን ከመሰረቱ ለማስተካከል የትምህርት ተቋማትን የጥራት ደረጃ ማስጠበቅ አንዱ የጥራት መመዘኛ ነው ብለዋል።

በክልሉ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለቁጥር የተገነቡ እንጂ ጥራታቸውን የጠበቁ አይደሉም ያሉት አቶ ግርማ፤ ይህም በትምህርት ጥራቱ ላይ አሉታዊ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል።

በክልሉ የትምህርት አገልግሎት እየሰጡ ከሚገኙ ከ27 ሺህ በላይ የቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት ውስጥ፤ አስር ሺህ 50 ትምህርት ቤቶች ላይ ባለፉት ሁለት ዓመታት የጥራት ምዘና ተደርጎባቸው 15 በመቶ የሚሆኑት ትምህርት ቤቶች መካከለኛ ጥራት የሚያሟሉ ሲሆን 85 በመቶ የሚሆኑት ለመማር ማስተማር ምቹ አይደሉም ሲሉ አብራርተዋል።

የትምህርት ቤቶችን የጥራት ደረጃ በማሻሻል የትምህርትን ጥራት ለማምጣት አገራዊ አጀንዳ ሊሆን እንደሚገባ አመላክተዋል።

በቤኒሻንጉል ክልልም ተመሳሳይ የትምህርት ጥራት ላይ ችግር የሚፈጥር የትምህርት ቤቶች ደረጃ መኖሩን የክልሉ ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኑረዲን ሙከታር አስረድተዋል።

ትምህርት ቤቶች ጥራታቸው ተሟላ የሚባለው ደረጃ አራት ሲደርሱ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በክልሉ የትምህርት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች ደረጃ አንድና ሁለት ላይ የሚገኙ ናቸው ብለዋል።

የትምህርት ጥራትን ለማምጣት የትምህርት ቤቶችን የደረጃ ጥራት ወደ ደረጃ ሦስትና አራት ለማድረስ እየተሰራ ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

# ዘላቂ ሰላምን ለማጽናት ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዳልነበር ይሆናል።

ደስታንም ሆነ ኃዘንን በቅጡና በወጉ ለማጣጣም ሰላም መሠረታዊና ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ እንደአገር ሰላምን ለማጽናት አገራዊ ምክክር እና የፍትህ ተቋማት ሪፎርም ጨማሮ ሌሎች በርካታ ሥራዎች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው። ተግባሩን ውጤታማ ለማድረግ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከህብረተሰቡ እና ከመንግሥት በርካታ ሥራዎች ይጠበቃሉ።

ሰላምን ለማጽናት በሚደረገው አገራዊ የምክክር ሂደት ውስጥ የአገር ሽማግሌዎች ሦስት አይነት ሚና እንዳላቸው የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ ብሌን ገብረመድህን ይናገራሉ።

እንደ ወይዘሮ ብሌን ገለፃ፤ የአገር ሽማግሌዎች በአገራዊ ምክክሩ ሦስት አይነት ሚና አላቸው። የምክክሩ ተሳታፊዎች ይሆናሉ፤ አጀንዳ ተሰብስቦ ከተመረጠ በኋላ በምክክር ሂደት የሰብሳቢነት ሚናን በመላበስ ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆን ያደርጋሉ እንዲሁም ከኮሚሽኑ የሚገኙ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ያደርጋሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ የህብረተሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን እና ሌሎች ጉዳዮች ምን እንደሚመስል ለኮሚሽኑ ያሳውቃሉ ያሉት ወይዘሮ ብሌን፤ ይህም አጀንዳዎችን በመፍጠር የምክክር ሂደቱ ሰላማዊ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል።

ህብረተሰቡም የተለያዩ ሚናዎች ይኖሩታል። እንዲያውም በቀጥታ ሲነገር የአገራዊ ምክክር ባለቤት ህብረተሰቡ ነው። ስለዚህ እንደአንድ ባለቤት በምክክሩ ሂደት መሳተፍ ይገባል። ለአገራዊ ምክክሩ አጀንዳ የሚሆኑ ጉዳዮችን በተቀመጡት አማራጮች መላክ ይኖርባቸዋል። ከዚህም ባለፈ የምክክር ሂደቱ ሰላማዊና ፍትሐዊ እንዲሆን እንደባለቤት መጠበቅ እንደሚኖርባቸውም ወይዘሮ ብሌን ያብራራሉ።

የእርቅና ሰላም ባለሙያና አማካሪ አቶ ጋረደው አሰፋ በበኩላቸው፤ ሰላምን ለማምጣትና ለማጽናት የሁሉም ተሳትፎ ያስፈልጋል። ሰላም የሚደረግ፣ የሚጠበቅ እና የሚያድግ ነው። ስለዚህ በሰዎች ዘንድ ሰላም ይደረጋል፤ የመጣው ሰላም ደግሞ ይጠበቃል፤ እየተጠበቀ ያለው ሰላም እንዲያድግ ይፈለጋል ብለዋል።

ሰላምን ለማጽናት የበርካታ ሰዎች ተሳትፎ የሚያስፈልግ ሲሆን፤ ሰላምን ለማበላሸት ግን የብዙ ሰዎች ተሳትፎ አያስፈልግም ያሉት አቶ ጋረደው፤ ሰላምን ለማጽናት፣ ለማስቀጠል እና በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርጽ ለማድረግ የአገር ሽማግሌዎች ሚና ከፍተኛ ነው ይላሉ።

የአገር ሽማግሌዎች በህይወት የሚንቀሳቀሱ መረጃዎች ናቸው። ምክንያቱም የአገር ሽማግሌዎች ያለፈውን ታሪክ እና አሁን እየተሰራ ያለውን ታሪክ ለሚመጣው ትውልድ ለማስረጽ ይሰራሉ። ስለዚህ የአገር ሽማግሌዎች የሰላም ጠባቂ ናቸው ማለት ይቻላል ብለዋል።

ያለፈው ትውልድ ስለሰላም ምን ተገነዘበ እና ምን ሰራ፣ የአሁኑ ትውልድ ስለሰላም ምን ማድረግ አለበት፤ የሚመጣው ትውልድ ደግሞ ከሰላም አንፃር ምን ግንዛቤ ይዞ ማደግ አለበት የሚለውን ለማሳየት ጠቃሚ ናቸው። ስለዚህ በአገር ሰላም እንዲሰፍን የአገር ሽማግሌዎችን አጥብቆ መያዝ ይገባል ብለዋል።

በሰላም ሚኒስቴር የሰላም ግንባታ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ዳንኤል በረደድ በአገር ሰላም ግንባታ የማህበረሰቡ ሚና ከፍተኛ ነው ባይ ናቸው። ስልጡን የምክክር ባህል ማጎልበት እና ችግሮችን በውይይት መፍታት፣ ለአካባቢው ሰላም መስፈን የባለቤትነት ስሜት መያዝና በማንኛውም የሰላም ግንባታ ተግባራት ላይ መሳተፍ ከአንድ ስልጡን ማህበረሰብ የሚጠበቁ ናቸው ይላሉ። የአካባቢን ሰላም እና ጸጥታ በሚያረጋግጡ ስራዎች ላይም የማህበረሰብ ተሳትፎ ከፍተኛ መሆን ይኖርበታል ይላሉ።

እየተከናወኑ ያሉ አገራዊ ዘላቂ የሰላም ባህል ግንባታና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ስራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የበኩላቸውን ሚና መወጣት አለባቸው ያሉት አቶ ዳንኤል፤ ዕድር፣ ዕቁብ፣ እና የመሳሰሉት ተግባራት ላይ ቢሳተፉ ማህበራዊ ግንኙነት ስለሚጠናከር የእርስ በእርስ ግጭቶችን ማስቀረት እንደሚቻል ጠቁመዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ አመራሮቻቸው እና አባሎቻቸው የሚያደርጉትን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በአገራችን የተጀመረውን የሰላም ግንባታ ማጠናከር ይኖርባቸዋል የሚሉት አቶ ዳንኤል፤ መንግስት ደግሞ የዜጎች ሕገ-መንግሥታዊ መብት ሳይሸራረፍ እንዲከበር ሊያደርግ እንደሚገባው ይጠቅሳሉ።

# በጎነት የዳበሳቸው ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ የስድስት ኪሎ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ መሰረት፤ ሌት ተቀን ከህይወት ጋር ግብግብ እየገጠሙ የዕለት ጉርስ ማሟላት ቢችሉም የሚኖሩበትን ደሳሳ ጎጇቸውን አድሰው ለመኖር ህይወት ዳገት ሆኖባቸው በጠባብና በፍሳሽ ቤት በምሬት ለመከረም ተገድደዋል።

በክረምቱ መባቻ የቤታቸውን የጣራ ፍሳሽ ለመከላከል ሸራና ፕላስቲክ በማልበስ ለመከላከል የሚያደርጉት ጥረት ፍሬ አልባ ሆኖ ቆይቷም። ታዲያ እኚህ እናት ጎጇቸውን በአዲስ ለመቀለስም ሆነ ለማደስ አቅም ማጣታቸውን በህዘን አንገታቸውን አቀርቅረው እንባ እየተናነቃቸው አውስተውናል።

ተስፋቸው ተመናምኖ፤ ኑሯቸው ከሃምሌ ሰማይ እጥፉን ዳምኖ፤ ከችግራቸው መላቀቅ ባለመቻላቸው ለዓመታት አንገት ደፍተው ፍሳሽ ቤታቸው ሲጨቀይ አዲስ የተስፋ ብርሃን ታየች። ተስፋ እሳቸው ቤት ጎራ ብላ በዘንድሮው የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ጠባብ ቤታቸው በእድሳት ሰፍታላቸው መኖር የሚችሉበት እድል መፍጠሯ ደስታቸውን ከልክ በላይ አደረገችላቸው።

ለተቸግረ ሰው ከንፈር የመምጠጥ እርዳታችንን አስወግደን በምንችለው የመርዳት ባህላችን እየጎለበተ፤ የኖረ የመረዳዳት ባህላችን እያደገ መጣና በክረምት



አቶ ያሬድ ይገለጡ



ወ/ሮ መሰረት ጉተማ



እማሆይ ሽቱ ሀሰን

የበጎ ፍቃድ አገልግሎትና ድጋፍ ላይ ዕሴት ጨመረበት። የአቅም ደካሞችና የአረጋዊያንን እንባ እያበሰ የመኖር ተስፋን እያለመለመ ዓመታትን ተሻገረ። ወይዘሮ መሰረትም እንደ ቋጥኝ ገዝፎ አንገት ካስደፋ ችግር ተላቀው በሞቀና በደመቀ ቤት ሊኖሩ የቀራቸው ጊዜ ጥቂት ነው።

ሌላኛው አቶ ያሬድ ይገለጡ ይባላሉ። በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ለ15 ዓመታት ያህል በጠባብና ጣራው በሚያፈስ ቤት ውስጥ ህይወትን ሳይታክቱ እየታገሉ የኖሩ ናቸው። በክረምት ወቅት ደሳሳ ጎጇቸው ዶፍ ዝናቡን መቋቋም አቅቷት በየአቅጣጫው ውሃውን በመልቀቅ ጤናማ እንቅልፍ ማግኘት እንዳይችሉ እንዳደረገቻቸው በትካዜ አጫውተውናል።

አቅማቸው ፈቅዶ እልፍኛቸውን ማደስ ባለመቻላቸው ያለውን ችግር ተለማምዶ መኖርን አማራጭ አድርገውት እያለ የመከነ ህልማቸውን ደግፎ የተስፋ ስንቅ እንዲሰንቁ የሚያደርግ አንድ ክስተት ተከሰተ። ክስተቱም በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ደሳሳ ጎጃቸው ሊታደስ በከንቲባዋ መጀመር መቻሉ ነው። ይህ ክስተት ከፍሳሽና ከጠባብ ቤት ሊያወጣቸው እንደሚችል ሲያስቡ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለፅ መቸገራቸውን ገልጸውልናል።

“ህመምተኛ በመሆኔ ከሰዎች በማገኘው ዕርዳታ ነው የምኖረው፤ በዚያ ላይ በህመም የሚሰቃይ ልጅ አለኝ። ይህን ልጅ ይዤ በጠባብ ቤት ውስጥ ከሌላ ሰው ጋር በጋራ እየኖርኩ ነው” የሚሉት እማሆይ ሽቱ ሀሰን የዚሁ ወረዳ ነዋሪና የችግሩ ገፈት ቀማሽ ናቸው።

በወጣትነታቸው ወጥተው ወርደው ያሳደጓቸው ልጆቻቸው ዛሬ ጉልበታቸው ሲደክምና በሽታ ሲያድርባቸው ምርኩዛቸው ባይሆኗቸው የሚላስ የሚቀመስም ለማግኘት አዳጋች ይሆንባቸው ነበር።

በዚህ ህመምና ሃሳብ ውስጥ እየተብሰለሰሉ ሳለ ቤታቸው በከተማ አስተዳደር ሊታደስ እንደሆነ ሲሰሙ የተሰማቸው ደስታ እጥፍ ድርብ ሆኗል። ተስፋን በሰነቀ ፈገግታ ደስታቸውን ገልጸውልናል። በእናትነት ግርማ ሞገሳቸውም እጅ እየነሱ ችግራቸውን ተረድተው ከችግራቸው ለማውጣት የተስፋ ፍንጣቂ ለዘሩላቸው አካላት ሁሉ ምርቃታቸውን ለግሰው ተሰናበቱን።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዘንድሮ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትን በተጠናከረ የበጎ አገልግሎት ስራ ለማሳለፍ አቅዶ እየሰራ ሲሆን፤ በርካታ በጎ ፈቃደኛ ባለሀብቶችና ወጣቶችም በዚህ ሥራ ላይ ለመሰማራት ከወዲሁ እንቅስቃሴ ጀምረዋል።

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# ተስፋ ፈንጣቂ የፈጠራ ሥራዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ትምህርት ቤቶች የነገ ተመራማሪዎችና ሳይንቲስቶች መፍለቂያዎች እንደመሆናቸው መጠን ለፈጠራ ሥራዎች ትኩረት ሰጥተው መስራት እንደሚጠበቅባቸው ይታወቃል፡፡ ለዚህም ለፈጠራ ሥራዎች ትኩረት በመስጠት በንድፈ ሀሳብ የሚሰጡ ትምህርቶች ወደ ተግባር እንዲለውጡ በማድረግ ተማሪዎች የፈጠራ ክህሎታቸውን እንዲያዳበሩና ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሰሩ በማበረታታት ማገዝ አለባቸው። አሁን በተለያዩ አጋጣሚዎች ከምንመለከታቸው አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች ለፈጠራና ለምርምር ሥራዎች ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቤቶችን ለዚህ ማሳያ አርገን መጥቀስ እንችላለን፡፡ በየዓመቱ የግልም ሆነ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤቶቹ የተሰሩ የፈጠራና የምርምር ሥራዎችን በክፍለ ከተማ ደረጃ ለውድድር እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ ከእነዚያ ውስጥ የተሻሉትና በውድድሩ ያሸነፉት የፈጠራ ሥራዎች ደግሞ በከተማ ደረጃ እንዲወዳደሩ በማድረግ የፈጠራ ሥራዎች በመደገፍ እንዲበረታቱ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በክፍለ ከተማ ደረጃ ሲካሄድ የቆየው ውድድር በቅርቡ ደግሞ በከተማ ደረጃ በአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት 8ኛው ከተማ አቀፍ “በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ የዳበረ ትውልድ ለሀገር ብልጽግና” በሚል መሪ ቃል አውደ ርዕይ ተካሄዷል፡፡ በአውደ ርዕዩ ከመንግስትና ከግል ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ተማሪዎችና መምህራን የተሰሩ የፈጠራ ስራዎች ለእይታ ቀርበዋል።


የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ካቀረቡት መካከል ተማሪ በረከት ጌቱ አንዱ ነው። የቤተል ሕዳሴ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪ እንደሆነ የሚናገረው ተማሪ በረከት በርከት ያሉ የፈጠራ ሥራዎችን ይዞ ቀርቧል። በረከት የባዩሎጂ፣ የኬሚስትሪ፣ የአይ ሲቲ እና የፊዚክስ ትምህርት ዘርፎች የሚመለከቱ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች ሰርቶ ለእይታ አቅርቧል፡፡ በኮምፒዩተር ለመቆጣጠር የሚቻል ታንክ፣ ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም የሚያስችሉ የፈጠራ ሥራዎች ለእይታ ካቀረባቸው ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ተማሪ በረከት በተለይ በፊዚክስ የትምህርት ዘርፍ ከሰራቸው የፈጠራ ሥራዎች አንዱን ስንመለከት የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሮቦት ነው፡፡ ሮቦቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ተደርጎ የተሰራ ሲሆን፤ በተለይ የአእምሮ ውስንነት ላለባቸው (ለኦቲዝም) ህሙማን ከፍተኛ አገልግሎት እንደሚሰጥ ነው የሚናገረው፡፡

አሁን ላይ በሀገራችን የአእምሮ ውስንነት ያለባቸው (ኦቲዝም) ህሙማን ሰዎች ለብቻቸው ወደ ተዘጋጀላቸው ማዕከል እንዲገቡ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን የሚያነሳው ተማሪ በረከት፤ ይሁን እንጂ ህሙማኑ ባሉበት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሆነው አስፈላጊውን ሁሉ የሚያሟሉላቸውን የሮቦት ሞግዚቶች ብንጠቀምላቸው የተሻለ አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ይናገራል፡፡ «ይህንን የሮቦት ፈጠራ ለመሥራት ያነሳሳው በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሲቸገሩ ሲመለከት የፈጠራ ችሎታውን ተጠቅሞ የሚችለውን ቢያደርግ ችግራቸውን በተወሰነ መልኩም ቢሆን መቅረፍ እንደሚችል በማሰቡ መሆኑን ይገልፃል፡፡

የሮቦት ሞግዚቱ የአእምሮ ውስንነት ላለባቸው ወገኖች ከሰዎች የተሻለ የተለያዩ አገልግሎቶችን ሊሰጥ የሚችል እንደሆነ የሚጠቁመው ተማሪ በረከት፤ ሮቦቱ በአማርኛ፣ በአፍን ኦሮሞ፣ በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች እንዲያወራና መልስ እንዲሰጥ ተደርጎ የተሰራ መሆኑን ይናገራል፡፡ የሰዎችን ስሜት (የተለየ ባሕሪ) ተመልክቶ ሙሉ በሙሉ በመቅዳት (ስካን) የአእምሮ ውስንነት ያለባቸው ወገኖች ከዚያ ስሜት ውስጥ እንዲወጡ የሚያደርጉ ሙዚቃዎችን፣ ፊልሞችና ታሪኮችን በማሳየትና በመንገር እንደሚያጫውት ነው ያብራራው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች ለምሳሌ በራሳቸው ላይ አደጋን ሊፈጽሙ ሲሉም ሆነ በሌሎች አካላት አደጋ ሲፈጽምባቸው ለሚመለከተው አካል ደውሎ በማሳወቅ በቀላሉ እንዲጠበቁ የሚያደርግ መሆኑንም ያስረዳል፡፡

ተማሪ በረከት እንደሚለው፤ ሮቦቱ ሌላም ተጨማሪ አገልግሎትን ይሰጣል፤ ለማስተማሪያነትም ያገለግላል፡፡ በተለይ ለሕጻናት በቀላሉ በጨዋታ እያዋዙ ለማስተማር ያስችላል፡፡ ተማሪዎቹ መምህሩ ከሚያስተምራቸው ይልቅ በሮቦት ቢማሩ የመማር ፍላጎታቸው እንዲጨምር



**የመንገድ ሳይና የቤት ውስጥ የጽዳት አገልግሎት መስጠት የሚችል የመኪና ሮቦት፤**

ያደርጋል ይላል፡፡ አሁን ላይ ሮቦቱ ሰላምታ መስጠትና ሲጠሩት ወደ ተጠራበት ቦታ መሄድ እንዲችል ተደርጎ ነው የተሰራ፡፡ ይህ የሮቦት የፈጠራ ስራ ከወዳደቁ ቁሶች የተሰራ ሲሆን፣ የሚሰራውም በባትሪ ነው። ባትሪው አንድ ጊዜ ቻርጅ ከተደረገ ቀኑን ሙሉ አገልግሎት መስጠት ይችላል።

የፈጠራ ሥራዎችን ከልጅነቱ መሞከር ደስ ይለው እንደነበር የሚናገረው ተማሪ በረከት፤ ይህ የሮቦት የፈጠራ ስራ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ በየጊዜው ለውጦች እያሳየና እያደገ መምጣቱን ይናገራል፡፡ በቀጣይም ይህንን የፈጠራ ስራ እያሻሻለ ለትልቅ ደረጃ እንደሚያበቃውና ሌሎች አዳዲስ ሥራዎችን ለመስራት ጥረት እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡ የፈጠራ ስራዎቹን እንዲህ ባለ በአውደ ርዕይ ማቅረብ ለቀጣይ ሥራዎች ከዚህ የበለጠ እንዲሰራ ሞራልና ጉልበት እንደሆነውም ይገልጻል፡፡

ሌላኛዋ የፈጠራ ባለሙያ ከእቴጌ መነን አዳሪ ትምህርት ቤት የመጣችው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዋ እየሩሳሌም ታደሰ ስትሆን፣ የወዳደቁና የማይፈለጉ ፕላስቲኮች በመጠቀምና በቀላሉ ከሚገኙ ነገሮች የተሰራ እጅ ለሌላቸው አካል ጉዳተኞች ጸጉራቸውንም ሆነ ገላቸውን መታጠብ የሚያስችል የፈጠራ ሥራ ነው ይዛ የቀረበችው፡፡

ተማሪ እየሩሳሌም እንደምትለው፤ ይህ የፈጠራ ስራ እጅ ለሌላቸው አካል ጉዳተኞች አገጫቸውን በመጠቀም ማብሪያና ማጠፊያውን ተጠቀመው ገላቸውን መታጠብ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ የፈጠራ ሥራ እጅ ለሌላቸው አካል ጉዳተኞች ካለምንም የሰው እርዳታ ሳሙናና የገላ መታሻ እንዲሁም ለጸጉር መታጠብና ማበጠር የሚሆን ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ያሟላ ሲሆን ፀጉራቸውንም ሆነ ገላቸውን በቀላሉ መታጠብ የሚያስችላቸው የፈጠራ ውጤት እንደሆነ ታብራራለች፡፡

የፈጠራ ስራው በቀላሉ ከማይፈለጉ ቁሳቁስ የተሰራ መሆኑን ተማሪዋ ጠቅሳ፣ ኢኮኖሚን ሳይጎዳ ተጠቃሚ መሆን ያስችላል፤ በጥቂት ውጪ የተሰራ ቢሆንም የሚሠጠው ጥቅም ብዙ ነው ትላለች። በቀጣይም ሌሎች የፈጠራ ሥራዎችንም ለመስራት እቅዳለች። እንደዚህ አይነት አውደ ርዕዮች ሲዘጋጁ ያላቸውን አቅም የሚያሳዩበትና በቀላሉ ለችግሮች መፍትሔ የሚያገኙባቸው ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ እድል የሚያመቻች መሆኑን ገልጻለች፡፡ አሁን በእንደዚህ መልኩ የቀረበው የፈጠራ ሥራ እየተሻሻለ ለአካል ጉዳተኞች ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ቢደረግለት ከፍ ባለ ደረጃና ጥራት መስራት እንደምትችል ተናግራለች፡፡

የጄኔራል ታደሰ ብሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሰኚ አማኑኤል በበኩሉ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች ይዞ ቀርቧል። ከእነዚህ ውስጥ ተንቀሳቃሽ የስልክ ቻርጅ (ፓወር ባንክ) እና የመኪና ሮቦት ይገኙበታል፡፡ ተማሪው የፈጠራ ሥራውን የሰራው ከተለያየ አገልግሎት ከማይሰጡ ቁሳቁስ ሲሆን፤ በተለይ የስልክ ኃይል መሙያው (ፓወር ባንኩ) ገጠራማ በሆኑ አካባቢዎች የሚሰጠው አገልግሎት ላቅ ያለ እንደሆነ ይናገራል። ፓወር ባንኩ አንድ ጊዜ ኃይል ካጠራቀመ በኋላ ሦስት ስልክ ኃይል መሙላት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሶ፣ ከስልክ ባትሪ በተጨማሪም የእጅ ባትሪ ኃይል ለመሙላት እንደሚያገለግል ይናገራል፡፡

ሌላው የፈጠራ ሥራው የመኪና ሮቦት ነው፤ የቤት ውስጥም ሆነ የመንገድ ላይ ቆሻሻን ለማጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ የፈጠራ ሥራ እንደ ቤት መኪና ሆኖ አገልግሎት መስጠት እንደሚችል ይናገራል፡፡ የመኪና ሮቦቱ አንድ መኪና ሊኖረው የሚገባው ቁስ በሙሉ የተገጠመለት እንደሆነም ነው የሚገልጸው፡፡

ተማሪ ሰኚ እንደሚለው፤ አሁን በአብዛኛው ለመንገድ ጽዳት ተሰማርተው የሚገኙት እናቶች ናቸው፡፡ ይህ የፈጠራ ሀሳብ መነሻ ያደረገው ደግሞ እነዚህን እናቶች ድካም መቀነስን ነው፡፡ የመኪና ሮቦቱን መንገድ ላይ በመልቀቅ እቤት ውስጥ ሆኖ በዘመናዊ መቆጣጠሪያ የመንገድ ጽዳት እንዲያጸዳ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሮቦቱ ቆሻሻን በመሳብ ወደ አንድ ማከማቻ ማድረስ ይችላል፤ በተገጠመለት ሴንሰር አማካይነት ሰውም ሆነ ሌላ ተሽከርካሪ እንዳይገጨው በመከላከል ያለምንም እርዳታ በራሱ የጽዳት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

በሌላ በኩል ቆሻሻን ከማጽዳቱ በተጨማሪ እንደ መኪናም ሆኖ ለሰዎች አገልግሎት መስጠት ይችላል። አሁን ላይ የተሰራው የመኪና ሮቦት የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ላይ ለማድረስና ለመመለስ በሰው የሚሽከርከር መሆኑን ጠቅሶ፣ በቀጣይ በሚገጠምለት ሶፍት ዌር አማካይነት በራሱ ቦታው ድረስ በሚሄድ የሚታዘዘውን ትዕዛዝ እንዲፈጽም ለማድረግ ማቀዱን ነው ተማሪ ሰኚ የሚናገረው፡፡

ተማሪ ሰኚ ይህንን የፈጠራ ስራ ለመስራት መነሻ ያደረገው እናቱ ሁልጊዜ ቤት ለማጽዳት የሚደርስባትን ድካም ነው፡፡ ፈጠራውን በቀላሉ ማጽዳት የሚችል ነገር መፍጠር አለብኝ ብሎ እንደጀመረ ጠቅሶ፣ እያሳደገ እስከ መንገድ ጽዳት እንዲደርስ እንዳደረገ ይገልጻል፡፡ የመኪና ሮቦቱን ፈጠራ ሥራ ለማሳደግና ወደተግባር እንዲገባ ለማድረግ ስፖንሰር የሚያደርጉ አካላት ድጋፍ እየጠየቀ ይገኛል፡፡ በትልቁ ሠርቶ ለውጤት እንደሚያበቃው ጽኑ እምነት እንዳለው ተናግሯል፡፡

“ይህ የመኪና ሮቦት የሰው ጉልበት ይቀንሳል፤ በቆሻሻ ምክንያት ለተለያየ በሽታ የሚጋለጡ ሰዎችን ከበሽታ ይታደጋል” የሚለው ተማሪ ሰኚ፤ የፈጠራ ውጤቶችን መስራቱ ከውጭ የሚገቡትን በአገር ውስጥ መስራት እንደሚቻል የሚታይበት በመሆኑ ሊበረታታ ይገባል ይላል፡፡ ይህንን የፈጠራ ሥራ ለማውጣት በብዙ ድካምና ልፋት ውስጥ እንዳለፈ በማንሳትም በዚህ ውስጥ ማለፉ ደግሞ ብዙ ትምህርት እንዲያገኝ በማድረግ ብርታትና ጥንካሬ እንደሆነውም ይናገራል፡፡

በጄኔራል ታደሰ ብሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የባይሎጂ መምህር የሆኑት መምህር ስዩም ጥሩነህ በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ላብራቶሪዎች ውስጥ በተለይ የኬሚስትሪ መምህራን የተለያዩ ኬሚካሎችን ቀይጠው የሚለዩበት ማሽን ስለሌላቸው ይህንን ችግር መነሻ በማድረግ የፈጠራ ሥራ መስራታቸውን ይናገራሉ። መምህር ስዩም የሰሩት የፈጠራ ስራ አሮጊ የቡና መፍጫ ማሽን በመጠቀምና ዲናሞ በማስገባት የፕላስቲክ የውሃ ኮዳዎችንና ሌሎችንም ቁሳቁስ በአንድ ላይ አቀናጅቶ በመጠቀም ኬሚካሎችን መቀየጥ የሚያስችል የፈጠራ ሥራ መስራት መቻላቸውን ያስረዳሉ፡፡

መምህሩ እንደሚሉት፤ የዚህ የፈጠራ ሥራ አገልግሎቱም አንደኛው “ሶዲየም ክሎራይድና ሲልቨር ናይትሬት” አንድ ላይ ቀላቅሎ ሲልቪር ክሎራይድ ለማግኘት የሚደረገውን ሂደት የሚያቀል ነው፡፡ ሁለተኛ አገልግሎቱ ደግሞ በሕክምና ተቋማት ላብራቶሪ ምርመራ ውስጥ ደም፣ ሽንት እና የመሳሳሉትን የላብራቶሪ ምርመራ ለማድረግ አስፈላጊውን ምርመራ የሚካሄደበት የደምም ሆነ ሌሎች የምርመራ አይነቶች ከተሰጡ በኋላ በአምስት ደቂቃ ውስጥ መመርመር ያለበት የደምም ሆነ የሌሎች ነገሮች የበሽታ መንስኤ በቀላሉ ለመለየት የሚረዳ ነው፡፡

የፈጠራ ሥራው አሁን ላይ በትምህርት ቤቱ ላብራቶሪ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ የሚናገሩት መምህሩ፤ እንዲህ አይነቶች የፈጠራ ውጤቶች ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን ትምህርት ወደ ተግባር ለመቀየር እንደሚያገለግሉ ይናገራሉ፡፡ በተለይ በእጅ መንካት የማይቻሉ ኬሚካሎችን ቀላቅሎ ለተማሪዎች በተግባር ለማሳየት የግድ የላብራቶሪ ውስጥ መገኘት ያለበት ቁስ ማግኘት ካልተቻለ ከባድ ስለሚሆን ለዚህ ችግር መፍትሔ ለመፈለግ የግድ ስለሚል ነው፡፡ ይህንን የፈጠራ ሥራ የወጣው ውጪ ዲናሞ ለመግዛት የዋለ ብቻ መሆኑን ተናግሯል

ተማሪ ኤልሮሄ ፊሊሞን፣ ለአለምታዬ ብርሃኑ እና እዩኤል ሞገስ የተባሉት የፋውንቴን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያቀረቡት የፈጠራ ውጤት ደግሞ የግብርና ሥራን የሚያቀልና ዘር የሚዘራ ሮቦት ነው፡፡ የፈጠራው ውጤት አውቶማቲክ የሆነ ዘዴን ተጠቅሞ ዘር ለመስራት የሚያስችል ሲሆን፤ ይህ የፈጠራ ሥራ በቀላሉ እስከ አስር ሄክታር መሬት ድረስ መዝራት የሚያስችል እንደሆነ ተወካያቸው ተማሪ ኤልሮሄ ይገልፃል፡፡ የፈጠራ ሥራው ዘር ከመዝራት በተጨማሪም ለመስኖ አገልግሎት፣ የተባይ መድኃኒት ለመርጨት፣ ምርቱን ለመሰብሰብ የሚያስችል የፈጠራ ቴክኖሎጂዎች የተገጠሙለት ሲሆን በቀጣይም ማረስ እንዲችል የሚያደርጉና ሌሎችም የፈጠራ ቴክኖሎጂዎች እንደሚገጠሙለት አስረድቶናል፡፡

“ይህንን የፈጠራ ሥራ የጀመርነው በሀገራችን ኋላቀር የሆነውን ግብርና ማዘመን ብንችል ድህነትን ለመቀነስ እንችላለን በሚል ሀሳብ ነው” የሚለው ተማሪ ኤልሮሄ፤ ተግባራዊ ስራ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ እያሻሻሉ እና እያሳደጉ የመጡት ብዙ ነገር እንዳለም አስረድቶናል፡፡ በቀጣይም የፈጠራ ሥራቸውን ከዚህ የበለጠ አሳድገው ለአርሶ አደሩ እንዲተላለፍና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ እንደሚሰሩም ይናገራል፡፡

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የፋይናንስና ግብዓት አቅርቦት - ለግብርና መዘመን

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ኢትዮጵያ ከሦስት ሺህ ዘመን በላይ ዘመናዊ ግብርና እና ቴክኖሎጂን አጣምራ ባለመጠቀሟ እና ዘመን ወለድ ግኝቶችን መጠቀም ባለመቻሏ ዛሬም አርሶ አደሮቿ በበሬ እያረሱ ሚሊዮኖችን ለመመገብ ደፋ ቀና እያሉ ነው። በአሁኑ ወቅትም 22 ከመቶ የሚሆኑት ዜጎች ከድህነት አለመውጣታቸው ሚስጥሩ ደግሞ የግብርና እና የግብርና ግብዓት አቅርቦት ላይ ብዙ ሥራ ባለመሰራቱ የመጣ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ግብርናን ማዘመን የህልውና ጉዳይ መሆኑ ባይካድም ሆኖም የጉዳዩን አሳሳቢነት ያህል ስራዎች በታሰበው ልክ አለመሰራታቸው አሁንም ትልቁ ፈተና ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ምሰሶ እና ዋነኛ ማጠንጠኛውና ከአገሪቱ ሕዝብ 80 ከመቶ የሚሸፍነው አርሶ አደሩ ወይንም የገጠር ሕዝብ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም አሁንም ከግብርና ግብአቶች አቅርቦትና ፋይናንስ ጋር የሚነሱ ችግሮች አሉ። ይህ ደግሞ አርሶ አደር ወደ ዘመናዊ ግብርና ካልገባ እና የግብርና ግብዓት በወቅቱ ካልቀረበለት ጠንካራ መሰረት ያለው መር ኢኮኖሚ መገንባት የህልም እንጀራ መሆኑ አይቀሬ ነው።

የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብት ለማሳደግ በሚደረገው ጥረትም አርሶ አደሮች ግብዓትና ፋይናንስ አቅርቦት ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ቢሆንም፤ ይህም ብዙ ፈተና የበዛበት ስለመሆኑ ይነገራል። በመላ አገሪቱ ከባንኮች ብድር እየወሰዱ ከሚገኙት ዜጎች ግማሽ ሚሊዮን እንደማይሆኑ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ለመሆኑ የፋይናንስ እና ግብዓት አቅርቦት ኢትዮጵያ ግብርና መዘመን የሚኖረው ሚና እስከምን ድረስ ነው?

ዶክተር ይትባረክ ግርማ በሰሜን ሸዋ ዞን የግብርና ባለሙያ ሲሆኑ፤ ትልቁ ችግርና ሲታሰብ የበርካቶች አረዳድ ከሰብል እርሻ ጋር የተያያዘ አድርጎ የመረዳት ዝንባሌ መሆኑን በመጠቆም ግብርና ግን አጠቃላይ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚመለከት መሆኑን ይጠቁማሉ።

በእንስሳት ሀብት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀዳሚ አገር ብትሆንም በተጠቃሚነት ዓይን ደግሞ በታችኛው እርከን ወይንም በሀብቷ ካልተጠቀሙት የምትመደብ አገር ናት። ይህ የሆነውም ለግብርና ያለን አረዳድ አሊያም ግብርናን እየተተገበረበት ያለው አካሄድ ከዘመኑ ጋር የሚመጥን አለመሆኑን ነው ይላሉ።

በኢትዮጵያ ግብርና የሥራ ዕድል በመፍጠር 70 ከመቶ በላይ ቢሆንም፤ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ በእርሻ እየለማ ያለው መሬት በጣም አነስተኛ ሲሆን ምርታማነቱም በዚያው ልክ ዝቅተኛ ነው። በሌላ ገፅታው ደግሞ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ወጪ በማድረግ የግብርና ምርቶችንና ግብዓቶችን ከሚሸምቱ አገራት ተርታ በቀዳሚነት ትመደባለች። በተመሣሣይ በእንስሳት ሀብት ከበርካታ ዓለማችን ክፍሎች ቀዳሚ ብትሆንም አሁንም ድረስ ለዜጎቿ በቂ ምርት ማቅረብ የማትችል አገር መሆኗን በመጠቆም፤ የዚሁ ሁሉ እክል መነሻው ለግብርና መዘመንና ግብዓት አቅርቦት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን ነው ባይ ናቸው።

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ከፍተኛ አቅም ያላት ቢሆንም፤ የተመረጡ ዝርያዎችን መጠቀም ላይ ብዙ ርቀት መጓዝ አልተቻለም። በአርሶ አደሩ እና አርብቶ አደሩ ዘንድም ያለው አተያይ በርካታ እንስሳትን ከቤት መኖራቸውን እንጂ በመጠቀም ደረጃ የሚኖራቸውን ፋይዳ በቅጡ አለመረዳት መኖሩን ያብራራሉ።

ግብርናው በሰብል እርሻ ዓይን ሲታይም ከእንስሳት ግብርና የተለየ ርቀት አልሄደም የሚሉት ዶክተር ይትባረክ፤ አንድ ዓይነት ሰብሎችን በአንድ መሬት ላይ ለተከታታይ ዓመታት መዝራትም ሌላው ግብርናው ያልተሻገረው ፈተና መሆኑን ይገልጻሉ። በሌላ በኩል ደግሞ አርሶ አደሩ ገበያ ተኮር ምርቶችን የማምረት ባህሉም ደካማ ነው። በብዛት ዕለታዊ ፍጆታን መሰረት ያደረገ የግብርና ሥርዓት መከተልም አንድ ይህ ዘርፍ ያልተሻገረው ማነቆ ነው ይላሉ። ለዚህ ሁሉ ችግር መነሻው ደግሞ ግብርና የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ እርሻ የሚለው እሳቤ የገዘፈ ክብደት የሚሰጠው መሆኑና ያለውን አቅም በቅጡ አለመረዳት ነው።

እንደ ዶክተር ይትባረክ ገለፃ፤ ለግብርናው ያለው አረዳድ ብቻ ሳይሆን ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚም የሚቀርበው የፋይናንስና ብድር አቅርቦትም እጅግ በጣም አነስተኛ እና ወደፊት የሚያሻግር አለመሆኑን ነው። በተለይም አርሶ አደሩ እና አርብቶ አደሩ ያለውን ጥሪት እንደ ማስያዣ በመጠቀም ግብዓቶችን አሊያም ደግሞ ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎችን የሚያገኝበት ስርዓት አለመዘርጋቱ የግብርናው ፈተና ነው፤ አገሪቱም ወደ ላቀ ደረጃ እንዳትሸጋገር ሸብቦ ይዟታል የሚል የፀና እምነት አላቸው።

በተለይም በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ሆነ እና እንስሳት ሀብት ላይ ለሚደርሰው ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሰራሽ አደጋዎች በፍጥነት የሚታደግ የኢንሹራንስ በኢትዮጵያ አለመተግበሩ ግብርና ባለበት እንዲረግጥ አስገድዶታል። ከዚህም በተጨማሪ አርሶ አደሩንና እና አርብቶ አደሩን የሚታደግ ስርዓት መዘርጋት አለመቻሉ እንደ አገር ከፍተኛ ኪሳራ እያመጣ መሆኑን ያብራራሉ።

ግብርናን ለማዘመን የሚሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎችም ለግብርና ጠብ የሚል በረከት እያመጡ አለመሆኑን የሚኮንኑት ዶክተር ይትባረክ፤ የምርምር ተቋማት የሚያወጧቸውን ምርምሮችና እና ግኝቶች ወደ አርሶ አደሩ የማድረስና የመተግበር ሂደቱ አዝጋሚ ነው፤ ቢደርስም አተገባበሩ ላይ የጋራ መረዳት አለመኖሩን ያብራራሉ። በምርምር ተቋማት የሚሠሩ ሥራዎችም ወደ ሕዝብ በፍጥነት አለመድረሳቸው ብቻ ሳይሆንም፤ በአርሶ አደሩ የመረዳትና የመተግበር አቅም ልክ የታሰቡ አለመሆናቸው ነገሮችን የባሳ ጥልፍልፍ ያደርጋቸዋል።

የግብዓት አጠቃቀም እና አቅርቦት ሰንሰለቱም በጣም ከፍተኛ ችግር ያለበት ስለመሆኑም ያስገነዝባሉ። ከዚህም በተጨማሪ የግብዓት በተመጣጣኝ ዋጋ እና ፍጥነት አለመቅረብ ሌላኛው ራስ ምታት ነው። አርሶ አደሩ አልፎ አልፎም ቢሆን ትርፍ ምርት አምርቶ ወደሚፈልገው አካባቢ ለማድረስ የገበያ መረጃ፣ መሰረተ ልማትና መሰል እጥረቶች አሉ የሚለው የዶክተር ይትባረክ ሃሳብ ነው።

የሥራ ፈጣሪውና ፋይናንስን ባለሙያው አቶ ያሬድ ኃይለመስቀል በበኩላቸው፤ በሁሉም መስክ የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት እንዲያድግ ከተፈለገ በግብርና ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ይጠቁማሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ የፋይናንስ ሥርዓቱ ሁሉንም ዘርፎች ማዕከል ባደረገ መልኩ ሥራ ላይ እየዋለ አለመሆኑን ይጠቁማሉ።በተለይም የፋይናንስ ተቋማት ብድር አሰጣጥ ሁሉን ያቀፉ ባለመሆናቸው ማደግ የሚገባቸው ዘርፎች በሚታሰበው ፍጥነት አለማደጋቸውን ይገልፃሉ።

በምዕራቡ ዓለም ያለውን ተሞክሮ ለአብነት የሚያነሱት አቶ ያሬድ፤ ዘርፍ ተኮር የሆኑ ባንኮች መኖራቸውን ጭምር ያብራራሉ። ለአብነትም ግብርናው ለማዘመን ሲባል ለግብርናው ዘርፍ ግብዓት የሚያቀርቡ ተቋማት በብዛት አሉ። የመኖሪያ ቤት ችግርን ለማቃለልም በዚያው ልክ የተቋቋሙ ባንኮች እና ሌሎች የፋይናንስ አማራጮች በብዛት ይገኛሉ። ይህም በየዘርፉ ሁሉን አቀፍ ዕድገት እንዲመጣ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ያብራራሉ። በኢትዮጵያም መለመድ አለበት ብለው ከሚያስቧቸው አሰራሮች መካከል የፋይናንስ ተደራሽነት በመላ አገሪቱ ገቢራዊ መሆን አለበት። በእርግጥ አገሪቱ ያለፈችባቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና የምጣኔ ሀብት ዕድገት እና የተለያዩ ሁኔታዎች በዘርፉ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለማሳደሩም በማስታወስ፤ እነዚህን ግን በሚቀጥሉት ዓመታት ማስተካከል ይቻላል ባይ ናቸው።

በኢትዮጵያም ያለው የፋይናንስ ሥርዓት እየተጠናከረ መምጣት እንዳለበት የሚናገሩት የፋይናንስ ባለሙያው፤ ከውጭ ፋይናንስ ጥገኝነት ለመውጣትም ትልቅ ትኩረት መስጠት እንዳለበት ይመክራሉ። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት ሁሉን ተኮር አገልግሎት የሚከተሉ ከሆነ እና ዘመናዊ አሰራሮችን የሚተገብሩ ከሆነ የአገሪቱን ዘርፈ ብዙ ችግሮች የማቃለል ዕድላቸው በእጅጉ የሰፋ ስለመሆኑም ይናገራሉ።

**ግብዓቶችን በወቅቱ ማቅረብ፣ ዘመናዊ አሰራሮችን መከተል፣ መሠረተ ልማቶችን ማሟላት እና ዘመናዊ የፋይናንስ ሥርዓት መትከል የኢትዮጵያን ዕድገት ከሚያፋጥኑትና የሚሊዮኖችን የአገሪቱን ዜጎች ሕይወት የሚለውጥ እንደሆነም ይመክራሉ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ሰለሞን ደስታ በበኩላቸው፤ በአገሪቱ ያሉ የፋይናንስ ተቋማት አትራፊነታቻው የላቀ ደረጃ ላይ ቢሆንም በሁሉም ዘርፎች ላይ በማገዝና በመደገፍ ላይ ግን የሚቀራቸው መሆኑን ይጠቁማሉ። ይህን ለማስተካከል ሲባልም እንደ አገር ዘርፈ ብዙ ተግባራት በመከናወን ላይ መሆናቸውን ይጠቁማሉ። የፋይናንስ ተቋማት በአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ የሚኖራቸው ሚና ቀዳሚውን ድርሻ የሚይዝ መሆኑን ያብራራሉ።በተለይም አካታች የሆኑ የባንኮች፣ ኢንሹራንሶችና አነስተኛ ገንዘብ ተቋማት በአገር ምጣኔ ሀብት ላይ በእጅጉ የላቀ ሚና አላቸው።እንደ ምክትል ገዢው ገለፃ ከሆነ፤ በአንድ አገር ውስጥ የሚዘወረው የፋይናንስ ሥርዓት አቃፊነትና ሁሉ አቀፍ መልክ ያለው ከሆነ የምጣኔ ሀብት እንዲመነደግ ብሎም ተወዳዳሪነት እንዲኖርም ያስችላል ይላሉ። እንደ አገር ሁሉም ሴክተሮች ወደላቀ ምዕራፍ ለማሸጋገር የፋይናንስ አቅም መጠናከር አለበት፤ ለዚህ ደግሞ የባንኮች፣ ኢንሹራንሶች እና ማይክሮ ፋይናንሶች ሚና የማይተካ አለፍ ሲልም የአንበሳው ድርሻ የሚይዙ ይሆናል። ብሔራዊ ባንክም እነዚህ ተቋማት ጤናማ የገንዘብ ፍሰትና አቅም ብሎም ትርፋማነትን መከታተል ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን ኢኮኖሚ ወደ ላቀ ደረጃ በሚያሸጋግሩ ሥራዎች ላይ እንዲያተኩሩ ምክረ ሃሳብ የሚሰጥ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ምሁራኑ እንደሚስማሙት፤ በአሁኑ ወቅት ግብርናው መለወጥ ካለበት ውጤታማ የሆኑ ምርምሮችን ማካሄድ፣ እንዲሁም ልማዳዊ አሰራር መቀየር አለበት። የተቋማት፣ ምሁራን፣ ተመራማሪዎች እና አርሶ አደሩ ትስስር መጠናከር አለበት። ወዲህ ደግሞ ግብርናን ለማዘመን የሚያግዙ መሰረተ ልማቶች በስፋት ሊከወኑ ይገባል። ለዚሁ የሚረዱ መስመሮችንና አሰራሮችንም ማጠናከር ይገባል ሲሉ ይመክራሉ።

አርሶ አደሩ ግብርናውን እንዲለውጥ አስፈላጊ ድጋፎችን እና ክትትል ማድረግ ተገቢ እንደሆነና ከቴክኖሎጂ ጋር ማላመድም ሌላኛው ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ይጠቁማሉ። ግብዓቶችን በወቅቱ ማቅረብ፣ ዘመናዊ አሰራሮችን መከተል፣ መሠረተ ልማቶችን ማሟላት እና ዘመናዊ የፋይናንስ ሥርዓት መትከል የኢትዮጵያን ዕድገት ከሚያፋጥኑትና የሚሊዮኖችን የአገሪቱን ዜጎች ሕይወት የሚለውጥ እንደሆነም ይመክራሉ።

በተለይም አካታች የሆኑ የባንኮች፣ ኢንሹራንሶች እና አነስተኛ ገንዘብ ተቋማት በአገር ምጣኔ ሀብት ላይ በእጅጉ የላቀ ሚና የሚኖራቸው በመሆኑ ለግብርናው ዘርፍ የሚያደርጉት ድጋፍ ሊበረታታ እና በልዩ ሁኔታ ሊታይ እንደሚገባውም ይጠቁማሉ። ግብርና በአጭር ጊዜ በማዘመን ከሚታወቁ እና በግብዓት አቅርቦትን የተፋጠነ አሰራር ካላቸው አገራትም ተሞክሮዎችና ልምዶችን መጋራትም ሌላኛው መፍትሄ ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ሆነ እንስሳት ሀብት ላይ ለሚደርሰው ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሰራሽ አደጋዎች በፍጥነት የሚታደግ የኢንሹራንስ አሰራር መተግበር ግብርናውን ለመታደግ ዓይነተኛ መፍትሄ ሲሆን፤ በዚያው ልክ ግብዓቶችን በወቅቱ ለአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ማቅረብ ቀዳሚው መፍትሄ እንደሆን ይመክራሉ።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## «ሴቶች በራሳቸው ማመን ሲጀምሩ ህልማቸውን እውን ማድረግ ይችላሉ»

**-የኬሚካል መሐንዲስ ቤተልሔም ደጁ**

አስናቀ ፀጋዬ

ማንም ሰው ቆሻሻን የሚፀየፍ ቢሆንም የእርሷ ግን የተለየ ነው፡፡ በፍፁም ቆሻሻ ማየት አትፈልግም። ቆሻሻ ካየች ጥላ ከመሄድ ይልቅ ታፀዳለች፡፡ የአካባቢ ጠበቃም ነች፡፡ ደግሞም ገጣሚ ናት፡፡ አካባቢ በተለያዩ ሰው ሠራሽ ምክንያቶች እንዲጎዳ አትፈልግም፡፡ ለዚያም ነው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቷን ከአካባቢ ጋር ቁርኝት ያለውን የትምህርት መስክ መርጣ ያጠናቸው፡፡

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች የራሷን ገቢ ለማግኘት ተማሪዎችን አስጠንታለች፡፡ ድንገት በተፈጠረ ስህተት በወጣ የሥራ ቅጥር ማስታወቂያ አጋጣሚውን ተጠቅማ በተመረቀችበት የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ሞያ አይደለም ለሴቶች ለወንዶች እንኳን ፈታኝ በሆነው የቆዳ ማምረት ሥራ መደብ ተቀጥራ ሠርታለች፡፡ የፋብሪካው ቁንጮ መደብ በሆነው የኮሜርሺያል ማናጀር ሥራ ላይ ተመድባም ኃላፊነቷን በሚገባ ተወጥታለች፡፡

በአንድ አጋጣሚ የተመቻቸ የማነቃቂያ ንግግር መድረክ ከአንድ የሥራ ፈጠራ ባለቤት ጋር እንድትገናኝ ዕድል ፈጥሮላታል፡፡ ይኸው ዕድል የራሷን እሴት በመጨመር አዲስ ምርት ይዛ ወደ ገበያ ብቅ እንድትል ረድቷታል፡፡ ይህንኑ አዲስ ምርት ይዛ ወደ ገበያ በስፋት ለመግባትም ቅድሚያ ኅብረተሰቡን የማገልገል መርህ ይዛ ብቅ ብላለች፡- የካባው ትሬዲንግ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ቤተልሔም ደጁ፡፡

ወይዘሮ ቤተልሔም ውልድትና እድገቷ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ነው፡፡ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለውን ትምህርቷን በቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ተምራለች፡፡ ሆኖም አባቷ ልጆቻቸው የተሻለ ትምህርት እንዲያገኙ በመፈለጋቸው እርሷም ከቤተሰቡ ጋር አብራ ወደ አዲስ አበባ መጥታ ከሰባተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በእውቀት ለህብረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትላለች፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ቤት ተምራ አጠናቃለች፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በጥሩ ውጤት በማጠናቀቋ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገብታ በኬሚካል ኢንጂነሪንግ በ1998 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪዋን አግኝታለች፡፡ በጊዜው ትምህርቱ በጣም ከባድ፣ ሥራ የማይገኝበትና ብዙ ተማሪዎችም የማይመርጡት የነበረ ቢሆንም እርሷ የምትወደው የትምህርት መስክ በመሆኑ በትጋት ተምራ በጥሩ ውጤት ማጠናቀቅ ችላለች፡፡ በዩኒቨርሲቲው በነበራት ቆይታም የተማሪዎች መማክርት ፕሬዚዳንት ሆና አገልግላለች፡፡ ከሴቶች ጉዳይ ጋር በተያያዘም በተለይ ሴቶች መብታቸው እንዲጠበቅ በርካታ ሥራዎችን ሠርታለች፡፡

ወይዘሮ ቤተልሔም ቀድሞውኑ ከአካባቢ ጋር በተያያዘ የመሥራት ፍላጎት ያላት በመሆኑ የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ትምህርት መስክን የመጀመሪያዋ ምርጫ አድርጋና ወዳው ነበር የተማረችው፡፡ በተለይ ደግሞ የፀዳ አካባቢን ከመፍጠር ጋር በተያያዘ የተለያዩ ሥራዎችን የመሥራት ጉጉቷ ለትምህርቱ ልዩ ፍቅር እንዲኖራት አድርጓል።

ከዩኒቨርሲቲ ከተመረቀች በኋላም በገቢ ራሷን ለመቻል ወዲያው ነበር ሥራ መፈለግ የጀመረችው፡፡ ሆኖም በተማረችበት የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ትምህርት መስክ በቀላሉ ሥራ ማግኘት አልቻለችም፡፡ ሥራ እስከታገኝ ድረስ ሌላ ሥራ መፍጠር ነበረባትና «ልጆች እናስጠናለን» የሚል ጽሑፍ በትንሽ ወረቀት ላይ አሳትማ በተለያዩ የግል ትምህርት ቤቶች አሰራጨች፡፡ በጊዜው አስር ልጆችን በማስጠናት በወር እስከ ሁለት ሺ ብር ድረስ ታገኝ ነበር፡፡ ይህ ገንዘብ በወቅቱ ትልቅ የነበረ ቢሆንም ታዲያ ቤተሰቧ በተለይ አባቷ የራሷን ሥራ ፈጥራ እንድትሠራ ከነበራቸው ፍላጎት የተነሳ የማስጠናቱ ሥራ ተቀባይነት አልነበረውም፡፡

የኋላ ኋላ ግን በተማረችበት የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ሞያ ሥራ ማግኘቷ አልቀረም፡፡ አዲስ አበባ ቃሊቲ አካባቢ የሚገኘው ባቱ ቆዳ ፋብሪካ የሥራ ቅጥር በጋዜጣ ማስታወቂያ አወጣ፡፡ ፋብሪካው ለወንዶች ብቻ የሥራ ቅጥር ማስታወቂያ ያወጣ ቢሆንም ጋዜጣው በስህተት ሥራው ለሴቶችም ለወንዶችም መሆኑን ጠቅሶ በማውጣቱ ይህን አጋጣሚ መጠቀም እንዳለባት ተረዳች። እናም ለመወዳደር አመለከተች፡፡

ማመልከቻዋን ካስገባች በኋላ ግን ሴት የሚለው



ነገር ፋብሪካውን ጥያቄ ውስጥ ከቶት ነበር፡፡ ስለዚህ የቃለ ምልልስ ፈተናውን ለማለፍና በቦታው ላይ ብቁ ሆና ለመታየት በሚገባ ራሷን ለመግለፅ በርካታ ጥረቶችን አደረገች፡፡ ጥረቶቿ ሁሉ ፍሬ አፍርተው ለቃለ ምልልስ ቀርባ ፈተናውን አለፈች፡፡ በዩኒቨርሲቲ በነበራት ቆይታ ስታደርጋቸው የነበሩ ሁለገብ እንቅስቃሴዎችም ፈተናውን አልፋ ቆዳ ፋብሪካውን እንድትቀላቀል ረድተዋታል፡፡

ቆዳ ፋብሪካውን እንደተቀላቀለች የትምህርት ማስረጃዎቿ በአብዛኛው የማኔጅመንት ሥራውን እንድትሠራ የሚያስችልና ለዚሁ የቀረበ በመሆኑ አለቃዋ አብራው እንድትሠራ ጥያቄ አቀረበላት፡፡ ነገር ግን የእርሷ ፍላጎት በተማረችበት የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ትምህርት መስክ የቆዳ አመራረት ሂደትና ቴክኖሎጂው ምን እንደሚመስል ለማየት ነበር፡፡ ለሴት የሚመቸው የቆዳ ፋብሪካው የሥራ ክፍል የመጨረሻ የቆዳ ማጠናቀቂያ ክፍል ቢሆንም እርሷ በብዛት ወንዶች የሚያከናውኑትንና ፈታኝ የሆነውን የቆዳ የመጀመሪያ ማምረት ሥራ ክፍልን መረጠች፡፡

በዚህ የሥራ ክፍል ውስጥ እያለች «አትችለውም» የሚል ቅሬታ ከፋብሪካው በኩል ነበርና በሳምንቱ ሥራውን በሚመለከት ሪፖርት እንድታቀርብ ተጠየቀች። ቀን ከሌት ሳትተኛ በሳምንቱ በሥራ ክፍሉ ያየቻቸውን እያንዳንዱን ሥራዎች ከትባና አርባ ሁለት ገፅ ሪፖርት ፅፋ ለአለቃዋ አቀረበች፡፡ አለቃዋም በሪፖርቱ ደስተኛ ነበር። እንዲያውም ሪፖርቱን በማየት በፋብሪካው የጥናትና ልማት ሥራ ክፍል ብዙ ሳትደክም እንድትሠራ ፍላጎት አሳደረ፡፡ እርሷም በዚህ የሥራ መደብ ላይ ለመሥራት ደስተኛ ነበረች፡፡

በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለች ነበር ትዳር የያዘችውና የፀነሰችው፡፡ ስለዚህ ሥራው በእርሷ ላይም ሆነ በልጇ ጤና ላይ ጉዳት እንደሚያስከትል በሃኪሞች ስለተነገራት በቆዳ ምርት ሂደት ጥቅም ላይ የሚውለውን ኬሚካል መራቅ ነበረባት፡፡ ከሌላው የፋብሪካ ሥራ ግን አልራቀችም፡፡ ወደ ቢሮ ሥራዎች መጥታ ሥራዋን ቀጠለች፡፡ አለቃዋም ገና ስትቀጠር ሊያስገባት የነበረውን የኮሜርሺያል ማናጀርነት የሥራ መደብ ሰጣት፡፡ ደመወዟም አደገ፡፡ ትራንስፖርትም ተመቻቸላት፡፡

በኮሜርሺያል ማናጀርነት የሥራ መደብ የቆዳ ፋብሪካውን ለአስራ አምስት አመታት አገልግላለች፡፡ መጀመሪያ በገባችበት የቆዳ ማምረት የሥራ ዘርፍ ደግሞ ለሁለት አመት ሠርታለች፡፡ ፋብሪካው እንዲያድግና ብቃቱ እንዲጨምር የበኩሏን አስተዋፅኦ አድርጋለች፡፡ በዚሁ የሥራ ሂደት ታዲያ አማራጮችን በማየት የማስተር ኦፍ ኮሜርስ ትምህርቷን ሕንድ አገር ከሚገኘው ኢንድራ ጋንዲ ዩኒቨርሲቲ በርቀት ተከታትላ በ2004 ዓ.ም አጠናቃለች፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ታዲያ ሁሌም በአእምሮዋ የሚመላለስ ጥያቄ ነበር፡፡ ይኸውም «በርግጥ ቤተልሔም የራሷን ህልም እየኖረች ነው?» የሚል ነበር። «የራሴ የምትለውና ወደራሷ ብታቀርበው ልታደርገው የምትችለው ነገር ምንድን ነው?» የሚል ቅርብ ነገር እንዳለም ፈለገች፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለች ነበር በአንድ የማነቃቂያ መድረክ ላይ ታድማ ህልማችሁን ግለፁ ስትባል «ኢትዮጵያን ንፁና አረንጓዴ በማድረግ አካባቢን ንፁህ ለማድረግ የሚተጋ ትውልድ መፈጠር አለበት» ብላ የመለሰችው፡፡

«የእኔ አስተዋፅኦ ቢሆንና ትንሽ ነገር መሥራት የምችልበትን አካባቢ መፍጠር ብችል» ብላ እንቅስቃሴ እያደረገች ባለችበት ወቅት በዚሁ የማነቃቂያ መድረክ አቶ አስናቀ በፍቃዱ ከተባለና መጥፎ ሽታ የሚያጠፋና ከእፅዋት የሚሠራ የፈጠራ ሥራ ይዞ በመድረኩ ከታደመ ሰው ጋር ተገናኘች፡፡ ምርቱ የአገር ውስጥ መሆኑ ደግሞ ለማወቅ ይበልጥ አነሳሳት፡፡ ስልክ ቁጥር ተቀብላ በማግስቱ ደወለች፡፡ ተቀራርበው ተወያዩ፡፡

እናም እንደ ኬሚካል ኢንጂነር ባለሞያነቷ በቅድሚያ የፈጠራ ሃሳቡን በማድነቅ መጥፎ ሽታ ማፅጃ ምርቶቹ ወደገበያ ወጥተው ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ቀለማቸውን ሳይቀይሩና ሳይበላሹ ረጅም ጊዜ የሚቆዩበትን የእሴት ጭመራና የላብራቶሪ ፍተሻ ሥራዎች ሠራች፡፡ ምርቱ በኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን በኩል ማረጋገጫ እንዲያገኝና ሕጋዊ እንዲሆንም አድርጋለች፡፡ የሥራ ፈጠራ ባለቤትነቱንም በ2015 ዓ.ም መግቢያ በአቶ አስናቀ በፍቃዱ ስም አስመዝግባዋለች፡፡ የምርት ናሙና ፍተሻም በተመሳሳይ አሠርታለች፡፡

ቀጥሎ ለአቶ አስናቀ የፈጠራ ሥራ የሚገባውን ክብር በመስጠትና ክፍያም በመፈፀም በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ካባው ጀኔራል ትሬዲንግን በጋራ በማቋቋም የመጥፎ ሽታ ማጥፊያ ምርቶችን ማምረት ጀመረች፡፡ በኋላ ላይ ደግሞ በትምህርት ያገኘችውን ሳሙና የማምረት እውቀት በመጠቀም ከሽታ ማጥፊያው ጋር አቀናጅታ የሚያፀዳ ብቻ ሳይሆን ሽታም ጭምር የሚያጠፋ የራሷን የልብስ ፈሳሽ ሳሙና፣ የመስታወት ማፅጃ ሳሙናና የዕቃ ፈሳሽ ሳሙና መፍጠር ችላለች፡፡

በተለይ ደግሞ የመስታወት ማፅጃ ፈሳሽ ሳሙናው ከማፅዳትና ሽታ ከማጥፋት ባለፈ ጀርሞችንም የሚገድል መሆኑ እሴት የተጨመረበት የፈጠራ ሥራዋን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ምርቱ ለቁስል ማፅጃም እንዲሆን በምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ፍቃድ እንዲያገኝ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ መጥፎ ሽታ ማጥፊያ ምርቶቹን ለማምረትም አገር በቀል ዛፎችና ቅጠላቅጠሎች ከገበሬዎች ተሰብስበው በግብአትነት ይውላሉ፡፡ ለልብስና ዕቃ ማጠቢያ ፈሳሽ ሳሙናዎች ማምረቻ ደግሞ ከውጭ አገር የሚገቡ የኬሚካል ግብዓቶች ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

ሥራውን በ50 ሺ ብር መነሻ ካፒታል አዲስ አበባ ፉሪ አካባቢ የጀመረው ካባው ትሬዲንግ በአሁኑ ጊዜ ካፒታሉ ወደ 800 ሺ ብር አድጓል፡፡ ለስድስት ሰዎችም የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በቀጣይም ምርቶቹን በማሳደግ ካፒታሉን ወደ ሁለት ሚሊዮን ብር የማሳደግ እቅድ ይዟል፡፡ ማሽኖችን ለመግዛትም በልማት ባንክ በኩል ብድር እንዲመቻች ሥራዎችን እየሠራ ነው፡፡ የሥራ ፈጠራው በገንዘብ እንዲደገፍም ለልማት ባንክ ጥያቄ አቅርቧል፡፡

ኅብረተሰቡ ከአካባቢ ጋር በተገናኘ ያለውን ግንዛቤ ለማስፋት ብዙ መሠራት እንዳለበት የምትገልፀው ወይዘሮ ቤተልሔም፤ ከዚሁ በተጓዳኝ ደግሞ ኅብረተሰቡ በአገር ውስጥ ምርት ላይ ያለውን በጎ ያልሆነ አመለካከት ለመቀየርና በምርቶቹ ላይ እምነት እንዲኖረው በብዙ መሥራት እንደምትፈልግ ትገልፃለች፡፡ ለዚህም መጀመሪያ ኅብረተሰቡን ማገልገል እንደሚገባ ትጠቅሳለች፡፡ በተለይ ደግሞ የአገር ውስጥ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ በማቅረብ እንዲገዛና በምርቶቹ ላይ ያለውን እምነት እንዲገነባ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ትጠቁማለች፡፡

ከዚህ አንፃር እርሷም ምርቶቹን ለጥቁር አንበሳና ዘውዲቱ ሆስፒታሎች፣ ለሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ፣ ለሕፃናት ማቆያ፣ በአዲስ አበባ ለሚገኙ ለተለያዩ የመንግሥት ትምህርት ቤቶችና ወረዳዎች በነፃ በማቅረብ ኅብረተሰቡ ምርቶቹን እንዲለማመድ ማህበራዊ ኃላፊነቷን እየተወጣች ትገኛለች፡፡

ምርቶቹ በአሁኑ ጊዜ በሸማቾች ዘንድ ተቀባይነትን እያገኙ መምጣታቸውን የምትጠቅሰው ወይዘሮ ቤተልሔም፤ በመጀመሪያ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶቹን ማቅረብና ኅብረተሰቡን ማገልገል እንጂ ትርፍ ማግኘት ተቀዳሚ ዓላማዋ እንዳልሆነ ትገልፃለች፡፡ በቀጣይ ደግሞ ሰዎች የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓታቸውን የሚያስተካክሉበት ሥርዓት እንዲዘረጋና ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበት አሠራር እንዲፈጠር የማድረግ ውጥን እንዳላት ትጠቁማለች፡፡

በዚሁ አጋጣሚ ወደቢዝነሱ ዓለም መቀላቀል ለሚፈልጉና የራሳቸውን ሀሳብ አመንጭተው ህልማቸውን እውን በማድረግ ራሳቸውን መለወጥ ለሚፈልጉ ሴቶች በቅድሚያ በራሳቸው ላይ እምነት ማሳደር እንዳለባቸው ትናገራለች፡፡ ሴቶች በራሳቸው ልክ ማመን ሲጀምሩ ሀሳባቸውን አመንጭተው ህልማቸውን እውን ማድረግ እንደሚችሉም ታስረዳለች፡፡ ለዚህም ሁሉም ሴቶች የተሰጣቸውን ጥበብ አውርደው ማለፍ እንዳለባቸው ትመክራለች፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

የዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን ከ30 አመታት በፊት የተከወኑ አገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮችን በብዛት ይዳስሳል። የደርግ መንግስት ወድቆ የኢህዴግ መንግስት ዙፋኑን ሲረከብ በአገር ደረጃ የተካሄደ የእርቀ ሰላም ጉባኤን አስመልክቶ የወጡ ዘገባዎች ምን ይመስሉ ነበር...? በጊዜው የአገሪቱ የውስጥ የፀረ-ሰላም ኃይል ከተባለው ኦነግ ጋር በተያያዘ ለፕሬዚዳንቱ መለስ ዜናዊ ከጋዜጠኞች የቀረበ ጥያቄ እንዲሁም መግለጫም ነበር። ያንን ሥርዓት አንደግመውም ይላሉ ፕሬዚዳንቱ ...ከዚሁ ጋር በተያያዘ ኦነግ በወቅቱ ዋና ጸሃፊው የነበሩትን ሌንጮ ለታን አባሯል። በሌላ በኩል ደግሞ የሲውዲን ዜጋን የዘረፉት ግለሰቦች ይፈለጋሉ፤ እነዚህና ሌሎችም ጉዳዮች ተካተዋል።

### "ያንን ሥርዓት በምንም አይነት መልኩ ተመልሶ እንዳይመጣ ሰብረነዋል"

-የፕሬዝዳንት መለስ ጋዜጣዊ መግለጫ

.......

ጥያቄ-"የእርቅና የሰላም ጉባኤ የተባለውን ምክንያት በማድረግ ኦነግ የሚካሄደውን ጦርነት ለ7 ቀን እንዲቆም ትዕዛዝ አስተላልፌአለሁ የሚል ዜና አሰረጭቷል። ይሄ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? የእርቅና የሰላም ጉባኤ የሕገ መንግስቱን ማርቀቅና የምርጫውን ሂደት ሊያደናቅፈው ወይም ፈጽሞ እንዳይካሄድ ሊያደናቅፈው ይችላል?

.............

መልስ- መልካም ኦነግ ጦርነቱን ለ7 ቀን አቁሜአለሁ የተባለው እኔ እስከማውቀው ድረስ ለ7 ቀን ብቻ ሳይሆን ለረዥም ጊዜ እንዳቆመ ነው። (አዲስ ዘመን ታህሳስ 17 ቀን 1986ዓ.ም)

### የሰላምና እርቅ የተባለ ጉባኤ ተከፈተ

በመሀላችን ያለው ሰፊ የአመለካከት ልዩነትን ከተጨባጭ ስምምነት እያደረስን የሚል ስጋት ያንዣበበበትና የጉባኤው ቅንጅት አለመኖር የታየበት የዕርቀ ሰላሙ ጉባኤ አጀንዳውን ቢያፀድቅም በቅደም ተከተሉ ላይ ከስምምነት አልደረሰም።

ጉባኤው ዶ/ር በየነ ጴጥሮስን በሰብሳቢነት፣ ዶ/ር ታየ ወልደ ሰማያትን ደግሞ በፀሐፊነት የመረጠ ሲሆን እንዲሁም አስራ አምስት አባላትን ለጉባኤው ሪፖርተርነት ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ከግል ፕሬስ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከስራ ከተወገዱ መምህራን እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲ ከተባረሩ ተማሪዎች ኮሚቴ ተመርጠዋል ። (አዲስ ዘመን ታህሳስ 17 ቀን 1986ዓ.ም)

### ኦነግ ሌንጮ ለታን አባረረ

-አቶ ሌንጮ ለታ እጃቸውን ሰጡ

(ኢ.ዜ.አ)- የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ምክትል ዋና ጸሃፊ የነበሩትን አቶ ሌንጮ ለታን ከትናንት ታህሳስ 14/1986ዓ/ም ጀምሮ ከግንባሩ ኃላፊነታቸው ያስወገዳቸው መሆኑን ትናንት አስታወቀ፡፡

የአቶ ገላሳ ዲልቦ የኦነግ ዋና ጸሐፊ ፊርማ እንዲሁም የግንባሩን ማህተም የያዘው መገለጫ እንዳመለከተው ከአሁን ወዲያ ሌንጮ ለታ ግንባሩን የማይወክሉና በኦነግ ስም ምንም አይነት መግለጫም ሆነ ተግባር ሊያከናውኑ እንደማይችሉ ሕዝቡም ሆነ የግንባሩ ደጋፊዎችና ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ እንዲያውቁልኝ ሲል ገልጿል፡፡

.............

ይሄው የግንባሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ መግለጫ እንዳመለከተው በአቶ ኢብሳ ጉተማ መታሰር ሳቢያ ኦነግ የሰላምና የእርቅ ጉባኤ ላይ ሳይሳተፍ መቅረቱን ገልጿል፡፡

### የኦነግ አመራር አባል ተያዙ

(ኢ.ዜ.አ)- አቶ ኢብሳ ጉተማ የኦነግ የአመራር አባል በድርጅታቸው በኩል ጦርነት እንዲካሄድ አሳውጀው ጉዳት እንዲደርስ ካደረጉ በኋላ አዲስ አበባ ገብተው በመገኘታቸው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የፖሊስ ሠራዊት ማዕከላዊ ቢሮ አስታወቀ። (አዲስ ዘመን ኅዳር 13 ቀን 1986ዓ.ም)

### የአሜሪካ መንግስት ስለ ኢትዮጵያ የአቋም ለውጥ አለማድረጉን ገለጸ

የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ሰላምና እርቅ ስለተባለው ኮንፈረንስ ያለውን አቋም አዛብቶ ለማቅረብ የተለያዩ የግል መጽሔቶችና ጋዜጦች የተቀነባበረ ዘመቻ በማድረግ ላይ ናቸው።

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ሚስተር ማርክ ባስ ሰሞኑን የሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫ የዘገቡት በርካታ የግል ጋዜጦችና መፅሄቶች አሜሪካ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ላይ ያላትን የእምነትና የድጋፍ ፖሊሲ የቀየረች አስመስለው ቢያቀርቡም በአሜሪካ በኩል አንዳችም የአቋም ለውጥ አለመኖሩን በዚያው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ አምባሳደሩ በተደጋጋሚ አረጋግጠዋል።

............

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ሙዳይ የተባለው ሳምንታዊ የግል ጋዜጣ በታኅሳስ 3 እትሙ ላይ እንደዘገበው የአሜሪካ መንግስት የታኅሳስ ዘጠኙን የሰላም እና የእርቅ ጉባኤ እንደ ታላቅ ቁምነገር በመመልከት የአቋም ለውጥ አሳይቷል ከሚል የሌለ ድምዳሜ ደርሷል። (አዲስ ዘመን ታኅሳስ 23 ቀን 1986ዓ.ም)

### በቁለም አውራጃ የዱር አራዊት አዝመራ አጠፉ

በወለጋ ክፍለ ሀገር በቁለም አውራጃ የዱር አራዊት ገበሬዎች የዘሩት አዝመራ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱት ገበሬዎች ለአብዮቱ በዓል አዲስ አበባ መጥተው በሰነበቱበት ወቅት መሆኑን የቁለም ወረዳ ገበሬ ማህበራት ተወካዮች ገለጡ።

በቁለም ወረዳ በየዱሩ የሚኖሩ የዱር አራዊት ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ከርከሮ፣ ጎሽ፣ አሳማና የአንበሳ መንጋ በሌሊት ከየደኑ እየወጡ የገበሬዎቹን አዝመራ ከመብላታቸውም በላይ በቤት እንስሳትና በሰውም ጉዳት ማድረሳቸውን የአውራጃው የገበሬ ማህበር ሊቀመንበር አቶ አሸብር ኩምሳ ገልጠዋል። (አዲስ ዘመን መስከረም 14 ቀን 1969ዓ.ም)

### የሲውዲን ዜጋን የዘረፉት ይፈለጋሉ

(ኢ.ዜ.አ)- አዲስ አበባ ላይ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በወረዳ 13 የቀይ መስቀል ተወካይ የሲውዲን ዜጋ ላይ የዘረፉ ወንጀል ፈጽመው በክትትል ከተያዙት ሌላ ለጊዜው ሀይሌ ግዛው የተባለ የቀድሞ አየር ወለድ ባልደረባና አስናቀ ተስፋዬ ከሚባለው ተባባሪው ጋር የተሰወሩ መሆናቸውን የክልል 11 ፖሊስ ኮሚሽን አስታወቀ።

በሲውዲናዊው ዜጋ ላይ በተፈጸመው ዘረፋ ከተካፈሉት መካከል የተወሰኑት ከዘረፏቸው ንብረቶች ጋር በፖሊስ ክትትል የተያዙ መሆኑን ኮሚሽኑ አስታውቋል።

( አዲስ ዘመን ሰኔ 13 ቀን 1986 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ

## ጣሊያን ግዙፉን የጎማ ፋብሪካ በቻይና መንግሥት ስተያዘ ኩባንያ አልሸጥም አለች

በቻይና መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደረው ፒሬሊ የተባለውን ግዙፉን የጎማ አምራች ኩባንያ እንዳይገዛ ጣሊያን አግዳለች። የጣሊያን መንግሥት የፒሬሊን ገለልተኝነት ለመጠበቅ የወሰድኩት እርምጃ ነው ብሏል። በቻይና መንግሥት የሚመራው ሲኖኬም የተሰኘው የኬሚካል ኩባንያ የፒሬሊ ጎማ ትልቁ ባለድርሻ ነው።

151 ዓመት የሞላው መቀመጫው ሚላን የሆነው የጎማ ኩባንያ 37 በመቶ ድርሻው በቻይናው ድርጅት የተያዘ ነው። ቤይዝንግ እና ምዕራባዊያን አገራት ውጥረት ውስጥ ናቸው። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደግሞ ይህን ለማብረድ ወደ ቻይና አቅንተዋል።

እሑድ ዕለት ፒሬሊ ባወጣው መግለጫ፤ የጣሊያን መንግሥት የፒሬሊ አለቃ ማርኮ ፕሮቬራ ንብረት የሆነው ካምፌን የተሰኘው ድርጅት ብቻ ነው ዋን ሥራ አስኪያጅ መምረጥ የሚችለው የሚል መመሪያ ማውጣቱን ይፋ አድርጓል። መግለጫ አክሎ ፒሬሊ ምንም ዓይነት የሥልጣን ለውጥ ሲያደርግ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ የመመርመር ኃላፊነት አለበት ይላል።

ባለፈው መጋቢት የቻይናው ኩባንያ በድርጅቱ ያለውን ድርሻ ማሻሻል እንደሚፈልግ ለጣሊያን መንግሥት ገልጾ ነበር። የጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ መንግሥት ለአገሪቱ ትልቅ ጥቅም አላቸው የሚላቸውን ድርጅቶች የሚጠብቅበት ማዕቀፍ አለው። በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2015 ፒሬሊ ሰባት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዩሮ በሆነ ዋጋ ለቻይናው ኬምቻይና እና ለካምፌን ተሽጦ ነበር።

ከስድስት ዓመታት በኋላ ኬምቻይና የቻይና ንብረት ከሆነው ሲኖኬም ጋር ጥምረት ፈጠረ። ከሁለቱ ድርጅቶች ባሻገር ሌላኛው የቻይና መንግሥት ንብረት የሆነው ሲልክ ሮድ ኢንቨስትመንት ፈንድ 9 በመቶ የፒሬሊ ድርሻ ያለው መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።






የአረብ ኢምሬትስ ፕሬዝዳንትና የኳታር ኤሚር

## አረብ ኢምሬትስ እና ኳታር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን አደሱ

አረብ ኢምሬት እና ኳታር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን አደሱ። ላለፉት ዓመታት ተቋርጦ የነበረው የተባበሩት አረብ ኢምሬት እና ኳታር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲቀጥል ስምምነት ላይ ተደርሷል። እንደ አረብ ኢምሬት ዜና አገልግሎት (ዋም) ዘገባ ከሆነ ሁለቱ አገራት በአል-ኡላ ስምምነት መሰረት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸው እንዲቀጥል ወስነዋል። የአገራቱ ግንኙነት የአረብ አገራትን ትብብር የማጠናከሩ አንድ አካል ነው ተብሏል፡፡

ይህን ተከትሎም የአረብ ኢሚሬትስ ፕሬዝዳንት ሼክ መሃመድ ቢን ዛይድ በኳታር ጉብኝት እያደረጉ ነው። በዚህ ስምምነት መሰረትም ኳታር በአረብ ኢምሬት አቡዳቢ ኤምባሲዋን እንዲሁም በዱባይ ደግሞ ቆንሱላ ጽህፈት ቤቷን ትከፍታለች። የተባበሩት አረብ ኢምሬት ደግሞ በኳታር መዲና ዶሀ ኤምባሲዋን እንደምትከፍት ተገልጿል።

የሁለቱ አገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መታደስ የአረብ አገራት ትብብር አካል ነው ተብሏል። አረብ ኢምሬት ከዚህ በፊት ከኢራን እና ቱርክ ጋር የነበራትን የሻከረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን ማደሷ ይታወሳል። ከኢራን ጋር ለብዙ ዓመታት የሻከረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የነበራት ሌላኛዋ አገር ሳውዲ አረቢያ በቻይና አሸማጋይነት ግንኙነቷን ማደሷ አይዘነጋም።

ከአረብ ሊግ ታግዳ የነበረችው ሶሪያ ከ12 ዓመታት መገለል በኋላ ወደ መድረኩ የተመለሰች ሲሆን ፕሬዝዳንት በሽር አላሳድ ከአንድ ወር በፊት በሪያድ በተካሄደው የአረብ ሊግ ጉባኤ ላይ መሳተፋቸውን አል ዓይን ዘግቧል።

# ትምህርት ቤቶችን በማሻሻል...

ከገጽ 5 የዞረ

ለምሳሌ፣ የትምህርት ሚኒስቴር የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ሪፖርት እንደሚያመለክተው፤ በጦርነት ምክንያት የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት «አዲስ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤት» የሚል የትምህርት ቤት ዲዛይን ተዘጋጅቶ እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም በጦርነት ከወደሙት 1 ሺህ 335 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተወሰኑትን ሥራ ለማስጀመር ጥረት ተደርጓል፡፡ ሌሎች ትምህርት ቤቶችንም መልሶ ለማደራጀት እና ወደ መማር ማስተማር ሥራው ለማስገባት ከውስጥም ከውጪም ካሉ ባለድርሻዎች ጋር በትብብር እየተሠራ ነው፡፡

ለዚህ አንድ ማሳያ የሚሆነው፣ ትምህርት ሚኒስቴር በጦርነት የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መልሶ በመገንባት እና ወደ ሥራ በማስገባት ሂደት ላይ ከየክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር ጥር 2014 ዓ.ም ላይ ባደረገው ውይይት ለመልሶ ግንባታ ሥራው ከ1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ መመደቡን ገልጿል፤ ይሄም በተለይ በጦርነቱ ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባቸውና ሙሉ በሙሉ የወደሙ በአማራ እና አፋር ክልሎች የሚገኙ 1 ሺህ 93 ትምህርት ቤቶች ግንባታ እንደሚያውለውም አስታውቋል፡፡

ይሁን እንጂ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአፋር ክልል ብቻ ከ700 በላይ ትምህርት ቤቶች ተጎድተዋል፤ በአማራ ክልልም ከአራት ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች በጦርነት ቀጣና ውስጥ ነበሩ፡፡ ይሄ ደግሞ ትምህርት ቤቶቹ ጣራና ግድግዳቸው ብቻ ሳይሆን፤ መሠረተ ልማታቸው እና የመማር ማስተማር ቁሳቁሳቸው (ቤተ ሙከራዎች፣ ቤተ መጽሐፍቶች፣ የአይ.ሲ.ቲ ቁሳቁሶች፣ ፕላዝማዎች እና ሌሎችም ቁሳቁሶች) አብረው ለጉዳት ተጋልጠዋል፤ ወድመዋልም፡፡

በትግራይ ክልል ያለውም ጉዳት በተመሳሳይ ደረጃ የሚገለጽ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የደረሰው ጉዳት ሲሰላ ደግሞ ለአብነት፣ በአማራ ክልል ብቻ በጦርነቱ የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት እና ለማደራጀት ከ20 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ነው የተለያዩ መረጃዎች የሚያመለክቱት፡፡

ይሄን መሰል እውነት ለማሳየት በሚል ሦስቱ ክልሎች በተለይም የአማራ ክልል እንደ ዋና ማሳያ ይነሳ እንጂ፤ በአንድም በሌላም ምክንያት በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎችና አካባቢዎች የትምህርት ቤቶች ደረጃ ጉዳይ እጅጉን አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ የትምህርት ጥራት ችግሮች መንስኤዎች ዘርፈ ብዙ ቢሆኑም፤ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ምቹ አለመሆናቸው ከመሠረታዊ ችግሮች አንዱና ዋነኛው ነው። ምክንያቱም ደረጃቸውን ያልጠበቁ ብቻ ሳይሆን ከደረጃ በታች ያሉ ትምህርት ቤቶች በኢትዮጵያ እጅጉን የበዙ ናቸውና ነው፡፡

ለአብነት፣ የትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ ሌሎች መንግሥታዊ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በአገራችን ከ49 ሺ በላይ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ከ86 በመቶ በላይ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ከ71 በመቶ በላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ-ልማቶች በተሟላ ደረጃ ስለሌላቸው ተማሪዎች በተጓደለ የትምህርት ከባቢ ውስጥ እንዲማሩ ተገድደዋል።

ይሄ ደግሞ በእነዚህ ደረጃቸውን ባልጠበቁ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን እውቀት፣ ክህሎትና የባህሪ ለውጥ ማምጣት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ትምህርት ቤቶች መሠረታዊ ለሚባሉት የትምህርት ቤት መሠረተ ልማቶች (ንጹሕ ውሃ፣ መፀዳጃ ክፍሎች፣ በቂ መማሪያ ክፍሎች፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፤ የስፖርት ሜዳ፣ መጻሕፍት፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ ቤተ-ሙከራ፣ ወዘተ.) እንኳን ባዕድ የሆኑ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፣ በአገሪቱ ካሉት ትምህርት ቤቶች 33 ነጥብ ሁለት በመቶ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ እንዲሁም 55 ነጥብ 67 በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው የንጹህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ያላቸው። ከዚህ ውስጥም 21 ነጥብ ሦስት በመቶ በአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም 49 ነጥብ አንድ በመቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቀጥታ የቧንቧ ውሃ ተጠቃሚ መሆናቸውን መረጃው ያመላክታል። የተቀሩት ትምህርት ቤቶች ምንም ዓይነት የውሃ አቅርቦት የላቸውም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ 37 በመቶ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም 43 በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ የመፀዳጃ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን መረጃው ያሳያል። ከኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት አቅርቦት ጋር በተያያዘም፤ 29ነጥብ አራት በመቶ አንደኛ እና መካከለኛና 74 ነጥብ አምስት በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ የሆኑት። ይህም ትምህርት ቤቶች በቴክኖሎጂ የተደገፈ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የትምህርት ክህሎትን እንዲያዳብሩ ለማድረግ የሚሠራውን ሥራ ፈታኝ ያደርገዋል።

ሌላው የትምህርት ቤቶቻችን ችግር የትምህርት ፋሲሊቲና ግብዓቶችን የሚመለከት ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም የትምህርት ቤቶችን ቁጥር ከማሳደግ አንፃር የሚያበረታታ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ይሁን እንጂ የትምህርት ቤት ቁጥር መጨመር በራሱ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ ትምህርት ቤቶቹ ስታንዳርዱን ጠብቀው እንዲመሠረቱ ከማድረግ አንፃር ሰፊ ክፍተት ያለ በመሆኑ ከግብዓት አንፃር መሠረታዊ የሚባል ክፍተት አለባቸው።

እነዚህ እና መሰል የትምህርት ቤቶች የደረጃ በታች መገለጫ እና የተማሪዎችን እውቀትና ክህሎት ከመገንባት አውድነት የመነጠል ችግር በዚህ መልኩ ከቀጠለ ትውልዱ ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ቀላል አይሆንም። ለዚህ አንዱ ማሳያ ደግሞ በባለፈው ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት የሚጠቀስ ነው፡፡ በመሆኑም ይሄንን ችግር ለመፍታት እና የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል በመንግሥት አቅጣጫ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህን ሥር የሰደደ ችግር በመንግሥት አቅም ብቻ ለመፍታት ቢታሰብ ከሦስት አስርት አመታት ያላነሰ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ይሄንንም መንግሥት የተቀበለው እና በሂደቱ የሕዝብን ተሳትፎ ማረጋገጥ ወሳኝ ሚና እንዳለው ግንዛቤ ተይዟል፡፡ ስለዚህ ይህን ሰፊ ችግር መፍታት የሚቻለው ሥርዓት ዘርግቶ በዘላቂነት የማኅበረሰብና የልዩ ልዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ቀጥተኛ ተሣትፎን ያማከለ ንቅናቄ በማድረግ እንደሆነም ታምኖበታል።

ከዚህ አንፃር የትምህርት ሚኒስቴር ባቀደው አገር አቀፍ ንቅናቄ መሠረት በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ የአካባቢው ማኅበረሰብ፣ የቀድሞ ተማሪዎች፤ ታዋቂ ግለሰቦች፣ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ ወዘተ. በትውልድ ቦታቸው፣ በተማሩበት ቦታ፣ በሚሠሩባቸውና በሚኖሩባቸው አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት በሚችሉት መንገድና መጠን አስተዋጽኦ በማድረግ አሻራቸውን የሚያሳርፉበት ሁኔታ ስለመመቻቸቱም ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት።

የንቅናቄው ዓላማም በየደረጃው ባለው ማኅበረሰብ እና ልዩ ልዩ አካላት ተሳትፎ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት ለማሻሻል የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራው በዘላቂነት እንዲቀጥል፤ እና ማኅበረሰቡ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ በመሠረተ-ልማት መሻሻል ሳይወሰን የመማር ማስተማሩን ሂደት በባለቤትነት እንዲደግፍ ማስቻል ነው፡፡ ከዚህ ከፍ ሲልም በየትምህርት ቤቶቹ ያሉ ችግሮችን በመገምገም እና ችግሮችን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ትምህርት ቤቶች ያለባቸውን ክፍተቶች በመፍታት የተማሪዎችን ውጤትና ሥነምግባር ማሻሻል ነው።

ይሄ እውን ይሆን ዘንድ ደግሞ፣ ሁሉም አካል የትምህርት ቤት መሠረተ ልማት ለትምህርት ያለውን ፋይዳ ሊገነዘበው ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ ችግሩን መገንዘብ እና ሁሉንም የትምህርት ባለድርሻ አካላት በማስተባበር ችግሮቹን መፍታት ካልተቻለ፤ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች መማሪያ ማዕከል ከመሆን ይልቅ መዋያ ብቻ መሆናቸው አይቀሬ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ የትምህርት ሥርዓቱን ምን ያህል እንደጎዳ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የ2014 ዓ.ም የተማሪዎችን የ12ኛ ክፍል ፈተና ውጤት ማየት ብቻ በቂ ነው። ስለሆነም የተለያዩ አማራጮችን በመፈተሽ የትምህርት ቤት መሠረተ ልማቶችን በስታንዳርዱ መሠረት ማሟላት ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ኃላፊነት ይሆናል።

በዚህ መልኩ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሻሻል ረገድ መሠረታዊ ከሚባሉት ከውሃ፣ መብራት፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ የኤሌክትሪክ እና ሌሎችም መሠረተ ልማቶች ባሻገር፤ ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮችን ማዕከል አድርጎ መስራት ከባለድርሻዎች ከሚጠበቁ ተግባራት አሉ፡፡ ከእነዚህ ሦስት ነጥቦች መካከል አንደኛው፣ ትምህርት ቤቶች በስታንዳርድ መሠረት የተሟላ ቤተ መጻሕፍት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

ምክንያቱም አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በግብዓት የተሟላና ስታንዳርዱን የጠበቀ የቤተ መጻሕፍት አገልግሎት የላቸውም። ያላቸውም ቢሆኑ በስታንዳርዱ መሠረት በግብዓት የተሟሉ አይደሉም። ተማሪዎች ደግሞ በክፍል ውስጥ ከሚሰጣቸው ትምህርት በተጨማሪ የተማሩትን ትምህርት በተሻለ ደረጃ እንዲገነዘቡና እንዲመራመሩ በስታንዳርድ መሠረት የተሟላ ቤተ መጻሕፍት ያስፈልጋቸዋልና ይሄንን ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ የቤተ-ሙከራ አገልግሎት ሲሆን፤ ይሄም ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን ትምህርት በተሻለ መልኩ እንዲረዱት ከማገዙም በተጨማሪ የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ የማገዝ፣ ንድፈ ሀሳቦችን የመገምገምና የመተንተን ችሎታቸውን የሚያበለጽግ ነው፡፡ በትምህርት ቤቶች የቤተ ሙከራ አገልግሎት መኖር ለቀጣይ የትምህርት እርከኖች የተዘጋጁ ተማሪዎች እንዲኖሩ ከማድረግ አንጻር ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም በአንደኛ ደረጃ ትምህርትም ሆነ በሌሎች የትምህርት እርከኖች ስታንዳርድ ውስጥ ለትምህርት እርከኑ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ያሟሉ ቤተ-ሙከራዎች እንዲኖሩ የሚጠበቅ ነው፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ግን አስፈላጊውን አገልግሎት ሊሰጡ የሚያስላቸውን ቁሳቁሶች አሟልተው የተገኙ ቤተ-ሙከራዎች ያሏቸው 59 በመቶ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ እንዲሁም 79 በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ እንደመሆናቸው፤ ይሄንን ገጽታ መቀየር የሁሉም ዜጋ ቀጣይ ትኩረት ሊሆን ይገባል፡፡


ሦስተኛው ነጥብ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን የሚመለከት ሲሆን፤ እነዚህ ማዕከላት መምህራን በሚያስምሩት የትምህርት ዓይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚያዘጋጁበትና ትምህርት ቤቱም ከአካባቢ ቁሳቁስ ከሚሠሩ አጋዥ የመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች በተጨማሪ የፋብሪካ ምርቶችን በመግዛት የሚያደራጁበት ማዕከል ናቸው፡፡ በመሆኑም መምህራን ከማዕከሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እየተዋሱ የሚያስተምሩትን ትምህርት ይበልጥ ተጨባጭ በማድረግ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ለማሳደግ የሚገለገሉበትን ዕድል መፍጠር ቀጣይ የትውልዱን ዕጣ ፈንታ መወሰን መሆኑን ተገንዝቦ መሥራት ይገባል፡፡

እንደ አጠቃላይ ዛሬ ላይ በአገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ውለው የሚገቡባቸው ስፍራዎች ሳይሆን፤ ተምረው፣ እውቀትና ክህሎት አግኝተው የሚመለሱባቸው ቦታዎች እንዲሆኑ ማድረግ የዛሬ ተግባር መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ይሄ ሲሆን በማኅበረሰብና በልዩ ልዩ አካላት አስተዋጽኦና ጥረት እያደጉ የመጡ መሠረተ ልማታቸውን (ንጹሕ ውሃ፣ መፀዳጃ ክፍሎች፣ በቂ መማሪያ ክፍሎች፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፤ የስፖርት ሜዳ፣ መጻሕፍት፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ ቤተ-ሙከራ፣ ወዘተ.) ያሻሻሉ ትምህርት ቤቶች በብዛት እንዲኖሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይሄ ሲሆን ደግሞ ልጆቻችን ከትምህርት ቤቶች ማግኘት የሚገባቸውን የእውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከትና ሥነምግባራዊ ሰብዕናን ማግኘት ያስችላቸዋል፡፡

በመሆኑም ዛሬ ላይ ከደረጃ በታች ያሉ ትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሻሻል ሂደት የምናስቀምጣት አንዲት ጡብ፤ በነገ የልጆቻችን ዕጣ ፈንታ ላይ የራሳችንን አሻራ የማኖር ኃላፊነታችን መሆኑን አምኖ መቀበል ይኖርብናል። ስለሆነም የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሻሻል ሂደት የራሳችንን አበርክቶ በማድረግ በነገ የልጆቻችን ዕጣ ፈንታ ላይ የምንወስንበትን አሻራ እናኑር፤ የዕለቱ መልዕክቴ ነው፡፡ አበቃሁ፣ ሰላም፤ ቸር እንሰንብት!

**በአገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ውለው የሚገቡባቸው ስፍራዎች ሳይሆን፤ ተምረው፣ እውቀትና ክህሎት አግኝተው የሚመለሱባቸው ቦታዎች እንዲሆኑ ማድረግ የዛሬ ተግባር መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ይሄ ሲሆን በማኅበረሰብና በልዩ ልዩ አካላት አስተዋጽኦና ጥረት እያደጉ የመጡ መሠረተ ልማታቸውን (ንጹሕ ውሃ፣ መፀዳጃ ክፍሎች፣ በቂ መማሪያ ክፍሎች፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፤ የስፖርት ሜዳ፣ መጻሕፍት፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ ቤተ-ሙከራ፣ ወዘተ.) ያሻሻሉ ትምህርት ቤቶች በብዛት እንዲኖሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይሄ ሲሆን ደግሞ ልጆቻችን ከትምህርት ቤቶች ማግኘት የሚገባቸውን የእውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከትና ሥነምግባራዊ ሰብዕናን ማግኘት ያስችላቸዋል**

# ስፖርት



# ሉሲዎች ለኦሊምፒክ ማጣሪያ ዝግጅት ተጠሩ

ዓለማየሁ ግዛው

በ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ጨዋታዎች የሴቶች እግር ኳስ የአፍሪካ ዞን የመጀመሪያ ዙር ማጣሪያ ጨዋታ ከቻድ ጋር የተደለደለው የኢትዮጵያ ሴቶች ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን (ሊሲዎቹ) ዝግጅታቸውን ቀደም ብለው በአዲስ አበባ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህም እንዲረዳው ዋናው አሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል ለ34 ተጫዋቾች ጥሪ አድርገዋል።

የ2024 የኦሊምፒክ ጨዋታዎች በፈረንሳይ መዲና ፓሪስ አስተናጋጅነት ሊካሄድ የአንድ ዓመት እድሜ ብቻ ቀርቶታል። ትልቁ የዓለም የስፖርት ድግስ በሁለቱም ፆታዎች ከ40 በላይ ስፖርቶችን አካቶ የሚካሄድ ሲሆን በርካታ ስፖርተኞችን በማሳተፍ ግንባር ቀደሙ መድረክ ነው፡፡ ለዚህም ከአዘጋጅ ሀገር ቅድመ ዝግጅትና ሽር ጉድ ጎን ለጎን በመድረኩ የሚሳተፉት ስፖርተኞችና አገራት የሚለዩባቸው የማጣሪያ ውድድሮች ከወዲሁ ይካሄዳሉ። በመሆኑም በተለያዩ የስፖርት ዲሲፒሊኖች ማጣሪያዎች በቅርቡ የሚካሄዱ ይሆናል።

አገራት እንደየደረጃቸው ማጣሪያ ከሚያካሄዱባቸው ስፖርቶች ውስጥ እግር ኳስ አንዱ ነው፡፡ ኢትዮጵያም በሴቶች እግር ኳስ በኦሊምፒክ ለመሳተፍ በአፍሪካ ዞን የማጣሪያ ጨዋታዋን ታደርጋለች፡፡ የአፍሪካ ሴቶች የእግር ኳስ ማጣሪያ ውድድሩ አራት ዙሮች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያ ዙር ማጣሪያ ከሐምሌ 3-11 2015 ዓ.ም ይካሄዳል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ሉሲዎቹ) የመጀመሪያ ዙር የማጠሪያ ጨዋታቸውን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከቻድ አቻው ጋር የሚያደርጉ ይሆናል። ሉሲዎቹ በዓለም አገራት የእግር ኳስ ደረጃ ከዓለም 125 ደረጃን ይዘው ሲገኙ ተጋጣሚያቸው ቻድ በበኩሏ በዓለም የእግር ኳስ ደረጃ ካልተሰጣቸው አገራት ተርታ ትመደባለች። የሁለቱ አገራት አሸናፊ በሁለተኛ ዙር ማጣሪያውን ከናይጄሪያ ብሔራዊ ቡድን ጋር የሚያከናውን ይሆናል፡፡



ሉሲዎች ለ2024 የኦሊምፒክ ጨዋታዎች የማጣሪያ ዝግጅታቸውን በአዲስ አበባ ያደርጋሉ፤

በአሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል የሚመሩት ሉሲዎች የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታቸውን በተሻለ ብቃት ለማለፍ ጠንካራ ዝግጅትን ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በአፍሪካ ጥሩ እግር ኳስን ይጫወታሉ ከሚባሉት ብሔራዊ ቡድኖች መካከል ተጠቃሽ የሆኑት ሉሲዎቹ፣ ለተሻለ ዝግጅትና ውጤት ወጣትና ልምድ ያላቸውን ተጫዋቾች በማካተት ዝግጅታቸውን ከዛሬ ይጀምራሉ። ተጫዋቾቹ ትናንት በአዲስ አበባ ጁፒተር ሆቴል ሪፖርት በማድረግ ልምምዳቸውን እንዲጀምሩም ተነግሯቸዋል።

አሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል ለሉሲዎቹ ጥሪ ሲያቀርቡ የሴቶች ፕሪሚየር ሊግ ቻምፒዮኑ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከበረኛ እስከ አጥቂ ብዙ ተጫዋቾችን በማስመረጥ ቀዳሚ ሆኗል። በአጠቃላይ ስምንት ተጫዋቾችን ማስመረጡም ታውቋል፡፡ መቻልና ሀዋሳ ከተማ እያንዳንዳቸው አምስት አምስት ተጫዋች በማስመረጥ ይከተላሉ፡፡

ብሔራዊ ቡድኑ አራት ግብ ጠባቂዎችን ያካተተ ሲሆን( ታሪኳ በርገና፣ ፍሬወይኒ ገብሩ፣ ቤተልሔም ዮሐንስና ፅዮን ግርማን) ጥሪ የተደረገላቸው ግብ ጠባቂዎች ሆነዋል። በተከላካይ ስፍራ በርካታ ተጫዋቾች ጥሪ የተደረገላቸው ሲሆን (ብዙአየሁ ታደሰ፣ ናርዶስ ጌትነት፣ ቤተልሔም በቀለ፣ ነፃነት ፀጋዬ፣ ቅድስት ዘለቀ፣ መንደሪን ክንድይሁን፣ ብዙአየሁ አበራ፣ ኤልሳቤት ታምሩ፣ ደመቀች ዳንኤል፣ ትዕግሥት ኃይሌና ድርሻዬ መንዛን) በቡድኑ ተካተዋል።

በአማካይ ስፍራ ዘጠኝ ተጫዋቾችን ያካተተው ጥሪ (ንቦኝ የን፣ መሳይ ተመስገን፣ መዓድን ሳህሉ፣ ፅዮን ፈየራ፣ ሕይወት ዳንጊሶ፣ ንግስት ኃይሉ፣ ራኬብ ዓለማየሁና ንጋት ጌታቸውን) አካቷል፡፡ የአጥቂ ክፍሉ ከተከላካይ ክፍሉ በመቀጠል ብዙ ተጫዋቾች የተካተቱበት ሲሆን አስር ተጫዋቾችን ይዟል፡፡ (ሎዛ አበራ፣አረጋሽ ካልሳ፣ አርያት አዶንግ፣ ረድኤት አስረሳኸኝ፣ ቱሪስት ለማ፣ ማርታ ወልዴ፣ ዓለሚቱ ድሪባ፣ ንግስት በቀለ፣ በሬዱ በቀለና እና ሴናፍ ዋቁማ) ጥሪ የተደረገላቸው የአጥቂ ስፍራ ተጫዋቾች ናቸው፡፡

ሉሲዎቹ በሁሉም የሜዳ ክፍል ጠንካራና ልምድ ያላቸው ኮከቦችን ያሰባሰቡ ሲሆን የቅድመ ማጣሪያውን የደርሶ መልስ ጨዋታ የማለፍ ግምትም አግኝተዋል። በኢትዮጵያ ሴቶች ፕሪሚየር ሊግ ከ5 ጊዜ በላይ የኮከብ ግብ አግቢነቱን መድረክ መቆጣጠር የቻለችውና በብሔራዊ ቡድኑም ትልቅ ስፍራ የሚሰጣት ሎዛ አበራን ጨምሮ አረጋሽ ካሳ፣ ሴናፍ ዋቁማ፣ አርያት አዶንግ፣ ቱሪስት ለማና ታሪኳ በርገና ያላቸውን የዳበረ ልምድ ተጠቅመው ለብሔራዊ ቡድኑ ውጤት የጎላ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡